ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 7፣ ነሐሴ 2007

## የሶስተኛ ዲግሪ መርኃ ግብር በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)



ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ2008 ዓ.ም አዲስ ዓመትን ጧሪ ካጡ አረጋዊያን እና አሳዳጊ ከሌላቸው ሕፃናት ጋር ሲያከብር

### የመሪነት ብቃት ለራዕይ 2017 ስኬት

አለባቸው አስፋው

### Code Switching as a classroom Discourse: Factional or Functional?

Yenus Nurie

### የዘመን አቆጣጠር እንዴት እንደሚቀመር ልብ ብለው ያውቃሉ?

ገጽ 8

### ቀና ቀናውን

ገጽ 10

### ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2007 ዓ.ም በከፊል (በፎቶ ማህደር)

ገጽ 16

እውነትን መፈለግና ስሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

ናይል
THE NILE

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


## ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

**የአማካሪ ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
አቶ አማረ ካሳው
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ
ቃለአብ ሞላ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
አለባቸው አስፋው
የኑስ ኑሬ
መኳንንት ከተማ

አትክልት ዳኛው

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ
ፋንታነሽ ላቀው

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ


ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# አዲሱ አመት የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ ለማሳካት ጠንክረን የምንሰራበት መሆን አለበት!

2007 ዓ.ምን ጨርሰን አዲሱን ዓመት 2008ን ልንቀበል እየተንደረደርን ነው፡፡ መቼም አዲስ አመት ሲመጣ ሁላችንም አዲስ እቅድ፣ አዲስ ሃሳብ፣ አዲስ ኑሮ… እንዲኖረን እንመኛለን፡፡ ይህ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ በአሮጌው ዓመት (2007 ዓ.ም) አቅደነው የተሳካልን ሌላ እቅድ ስናቅድ ያልተሳካልን ደግሞ በአዲሱ ዓመት ደግመን እናቅዳለን፤ ካልሆነም ሌላ አዲስ እቅድ ይዘን ጉዞ እንጀምራለን፡፡

ከእቅድ ጋር ተያይዞ ባለሙያዎች እንደሚናገሩት እቅድ በዓመት አንዴ የሚታቀድ መሆን የለበትም፡፡ አንድ ሰው በህይወት ሲኖር ብዙ አላማ ስለሚኖረውና ይህንንም አላማ ለማሳካት የዓመት፣ የወራት፣ የሳምንታትና የቀናት እቅድ ያቅዳል፡፡ አዲስ ዓመት ሲመጣ የምናቅደው እቅድ ከላይ እንደተጠቀሰው ከተከፋፈሉት እቅዶች መካከል መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ አንዱ ዓመት አልቆ ወደ ሌላው ዓመት ስንሸጋገር አዲስ እቅድ ማውጣት ብዙም እንደማያስኬድ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ከአፍሪካ አስር ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን ቆርጦ ተነስቷል፡፡ ይህን ራዕይ እውን ለማድረግ እቅድ በማውጣት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ የተለያዩ ክፍሎችም በሥራቸው የሚሠሯቸውን ሥራዎች በማቀድ እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ በ2008 በጀት ዓመት ራዕይ ጥበብ 2017ን ለማሳካት የአምስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ በማቀድ ሥራውን ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ እቅዱን ለማሳካት ዋነኛው የለውጥ አካል የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መሆኑ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ተማሪዎች፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ መምህራንና አመራሩ የተያዙትን እቅዶች ከግብ ለማድረስ በጋራ መረባረብ ይጠበቅብናል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በአዲሱ አመት የዓመት፣ የወራት፣ የሳምንታትና የቀናት እቅድ በማዘጋጀት የራሱን እቅድ ከዩኒቨርሲቲው ራዕይና እቅድ ጋር በማስማማት ጠንክሮ መስራት ለተያዘው የስኬት መንገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

እቅዳችንን ከግብ ለማድረስ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በተሰማራበት የስራ መስክ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይኖርበታል፡፡ ተጠያቂነትና ግልጽነት የተሞላበት አካሄድ በመከተል ስኬትን ለመጎናጸፍ ጠንክረን መስራት አለብን፡፡ ባለፈው አመት የተገኙ ስኬቶችን የበለጠ በማጠናከር እንዲሁም የታዩ ችግሮችንና ተግዳሮቶችን በመለየትና እንዳይደገሙ ከስራቸው በማድረቅ የአዲሱን አመት እቅድ መስመር ማስያዝ ይኖርብናል፡፡

እያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እቅዶቹን ከግብ ለማድረስ ከእኔ ምን ይጠበቃል? የእኔ ድርሻ ምንድን ነው? ከምሠራበት የሥራ ክፍል ምን ይጠበቃል? ተግዳሮቶች ካሉ እንዴት መፍታት ይቻላል? እነዚህንና ተመሳሳይ የሆኑ መሰረታዊ ጥያቄዎችን በማንሳት እራሱን ዝግጁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

"ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሀኒቱ" ይላሉ አባቶቻችን ሲተርቱ አብሮ የመሥራት ጥቅምን ሲያስረዱ፡፡ የተቋሙን ራዕይ ለማሳካት በጋራ ማቀድ፣ በጋራ መሥራት፣ በጋራ ውጤታማ መሆን ወሳኝ ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲው የ2008 ዓ.ም እቅድ የሁላችንንም ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ተባብረን መስራት ይኖርብናል፡፡ አዲሱ አመት ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ስኬታማ እንዲሆን ጠንክረን የምንሰራበት መሆን አለበት፡፡

መልካም የስራ ዘመን ይሆንልን ዘንድ የዝግጅት ክፍላችን ይመኛል!

## ቁልፍ መልዕክት

# የሶስተኛ ዲግሪ መርኃ ግብር በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ዩኒቨርሲቲያችን የመጀመሪያውን የአምስት አመት የራዕይ ጥበብ 2017 ጉዞ በማጠናቀቅ የሁለተኛውን አምስት አመት ስትራቴጂካዊ ዕቅድ መተግበር መጀመሩ ይታወቃል፡፡ ዩኒቨርሲቲውን የምርምር ዩኒቨርሲቲ የማድረግ ጉዟችን እንዲሳካ የሚያደርጉ ስትራቴጂካዊ ስልቶች ለይተንና ማህበረሰቡ እንዲጋራው አድርገን የምንሠራቸው ተግባሮች ዋነኛ የርብርብ ማዕከሎች ናቸው፡፡ በዚህ አጭር ጽሑፍ ከምንተገብራቸው ስትራቴጂካዊ ስልቶች አንዱ የሆነውን የሶስተኛ ዲግሪ መርኃ ግብር የማስፋፋትና የማጠናከር ስልት በአጭሩ በማቅረብ ማህበረሰባችን እንዲወያይበት መነሻ ማድረግ ነው፡፡ ደጋግመን እንደገለጽነው የምርምር ዩኒቨርሲቲ መገለጫዎች ከሚባሉት ውስጥ ግንባር ቀደሞቹ የድህረ ምረቃ መርኃ ግብር ተማሪዎችና መርኃ ግብሮች ማደግ፣ በየአመቱ ከ100 በላይ የሚሆኑ የ3ኛ ዲግሪ ተመራቂዎች መኖር፣ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ግማሽ የሚሆኑት መምህራን የ3ኛ ዲግሪ ያላቸው መሆንና በታወቁ ህትመቶች የሚታተሙ ግኝቶች ማደግን ያካትታል፡፡

ከእነዚህ ወሳኝ የመስመራችንን ስኬት የሚለኩ መስፈርቶች ለማሟላት የሚያስችለው ዋነኛ ተግባር የ3ኛ ዲግሪ መርኃ ግብር ማጠናከርና ማስፋፋት ነው፡፡ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የማህበረሰብ ችግር የሚፈቱ ሀሳቦችንም ሆነ አዲስ የሀብት ምንጭ የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎች የሚፈጠሩት በዋነኝነት የ3ኛ ዲግሪ ተማሪዎችን በማሳተፍ ነው፡፡ በ3ኛ ዲግሪ የሚማሩ ተማሪዎች ከዕድሜያቸው ጋር በተያያዘና ሁሉንም በመስኩ ያሉ መሠረታዊ ንድፍ ሀሳቦችንና ተግባሮችን ለመገንዘብ በሚያደርጉት ግፊት አዲስ ሀሳብ የማፍለቅና የነበረውንም እሳቤ የማሳደግ ዕድላቸው የሰፋ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ነባር ተመራማሪዎች ያላሰቡትን ጉዳይ የማሰብና የመቀመር አቅም ይፈጥራሉ፡፡ እንዲህ አይነት ጉዞ በእኛ ዩኒቨርሲቲ ተጨባጭ ሁኔታ 3ኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ለማፍራት ብቻ ሳይሆን የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ያደረገና ለማህበረሰብ ዕድገት የሚበጅና ለእኛ የሚሆን ሀሳብና ቴክኖሎጂ የመቀመር አቅማችን ለማሳደግ ነው፡፡

ለማይመራመር/ለማትመራመር መምህር/ት ማስተማር እጅግ እንደሚያዳግት ይታወቃል፡፡ የ3ኛ ዲግሪ ማስፋፋት ስራችን የመምህራኖቻችንን የመመራመርና ቴክኖሎጅ የመቀመር አቅም ብቻ ሳይሆን የማስተማር ክህሎታቸውንም ያሳድጋል፡፡ የሚያስተምሩት ነገር ተጨባጭነት ያለውና ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተዛመደ አድርገው የማስተማር ዕድላቸውን ያሰፋል፡፡ በእነዚህ አይነት መምህራን የተማሩ ተማሪዎች ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በተግባር የሚይሳዩ ይሆናሉ፡፡ ጥራት ያለው ትምህርት ልናረጋግጥ የምንችለውም በዚህ አግባብ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች አኳያ የ3ኛ ዲግሪ መርኃ ግብር ማጠናከርና ማስፋፋት ስራችንን ስንመዝነው የራዕያችን ማስፈፀሚያ ዋነኛ ተግባር መሆኑን እንረዳለን፡፡ ስለሆነው በሚቀጥለው የራዕይ ጥበብ የአምስት አመት ዘመን ይህን ስትራቴጂ በፍጥነትና በጥራት የምናሳካበት ሁኔታ ላይ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብና አጋር አካላት ልንነጋገርበትና በየጊዜው ሀሳባችንን እያጠራን ልንጓዝ ይገባል፡፡ በተለይ ምሁራኖቻችን ሀሳባቸውን በይፋ አስቀምጠው የሚገጥሟቸውን ችግሮች ልንወያይባቸውና ልንፈታቸው የግድ ይለናል፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!!!

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

# አበይት ዜናዎች...

## መረዳዳትና መደጋገፍ አገራዊ ጠቀሜታው የጐላ መሆኑ ተገለፀ

በየማነ ገብሩ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ2008 ዓ.ም አዲስ ዓመትን ጧሪ ካጡ አረጋዊያንና በተለየ መልኩ ለችግር ተጋላጭ ከሆኑ ሕፃናት ጋር አከበረ፡፡ በበአሉ ላይ ከምሳ ፕሮግራም በተጨማሪ ከባሕር ዳር ከተማ ለተወጣጡ አረጋዊያን የአልባሳት እና አሳዳጊ ለሌላቸው ሕፃናት የመማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የውጭ ግንኙነትና ፓርትነርሽፕ ዳይሬክተር አቶ ሞገስ አብርሃ አረጋዊያንና አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናትን ለማበረታታትና ድጋፍ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ዝግጅት መሆኑን ጠቁመው ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች በተጨማሪ በተለያየ ምክንያት ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን በመደገፍ ማሕበራዊ ሀላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡አቶ ሞገስ አክለውም ዩኒቨርሲቲው ለምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት በሰጠው ልዩ ትኩረት የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት በርካታ ስራዎች እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸው ለወደፊትም ይህንኑ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ የመደጋገፍና የመረዳዳት እሴቶች ባለቤት የሆነች ሀገር በመሆኗ ይህንን ማሕበራዊ እሴት ማጐልበትና ማጠናከር ጠቀሜታው የጐላ በመሆኑ ይህ የአረጋዊያንና ወላጅ አልባ ሕፃናት ድጋፍ የመስጠት በጐ ተግባር ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ የበአሉ ተሳታፊዎች ጠይቀዋል፡፡ ሌሎችም ይህን ተሞክሮ በመውሰድ ድጋፍ የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የመደገፍ በጐ ተግባር እንዲተገብሩ ተጠቁሟል፡፡

በዕለቱ ስለ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፣ ስለ ባህላዊ አልባሳትና ስለ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የተፃፉና የተነገሩ ትፊታዊና ታሪካዊ ሥነ-ጽሑፎች በምሁራን ትንታኔ የቀረበ ሲሆን አዝናኝ የሆኑ የሙዚቃ ዝግጅትም ቀርቧል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው ከበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማህበራት ጋር በትብብር እየሠራ ነው

በአበባ ሐብቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ከአረንጓዴ አካባቢ ለሁሉም ልማት ማሕበር ጋር በመተባበር የችግኝ ተከላ አካሄደ፡፡

የአረንጓዴ ልማት ማሕበር የማሕበሩ ሥራ እስፈፃሚ አባልና የሂሳብ ሹም የሆኑት አቶ ሙሉጌታ ፀጋዬ እንዳሉት የልማት ማሕበሩ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማሕበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ክፍል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የተራራ የተቀናጀ ልማት፣ የመድሐኒት እፅዋት ልማትና ተያያዥ የማሕበሩ የገቢ ምንጭ ስራዎችን ለመደገፍና ዩኒቨርሲቲውም ለተማሪዎችም ሆነ ለተመራማሪዎች የተራራ ልማቱን ሲጠቀሙ የጋራ መግባባት ተፈጥሮ ወደ ሥራ በመግባት የፕሮጀክት ተግባር ሥራ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልፀውልናል፡፡

በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 16 ልዩ ስሙ የድባንቄ ተራራ የተቀናጀ የተራራ ላይ የአፈር ውሃ ጥበቃና ልማት ሥራ የበጐ አድራጐት ድርጅት ከመንግስት ተቀብሎ በሚያለማው ከ3-5 ሄክታር መሬት ላይ የእርጥበት አቀባ ሥራ ማለትም 3ሺህ ሜትር ሥራ ሰርቷል፡፡ ለመድኃኒትነት ያላቸውን እፅዋት ተክሎችን ለማላመድ ለማባዛት ለተጠቃሚዎችለ እና እንደ ምርምር ለመጠቀም በተራራው ላይ አንድ መለስተኛ ለመድሀኒት እፅዋት ማፍያ መሬት በማዘጋጀት ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በተጨማሪም የተራራ ልማቱን በዘላቂነት ለመጠበቅና ለመንከባከብ የተራራውን አጥር በስነ-ህይወታዊ ዘዴ የማጠር ሥራ ተሰርተዋል፡፡ ለዚህም የዋርካ ችግኝ እና የኮሽሽል እንጨት የመትከል የሳስፓንያ ዘሮችን 12 ኪ.ግራም የእሾህ ዘር በመዝራት ማጠናከር ለልማቱ የሚያገለግል በአንድ ቦታ የውሃ ማሰባሰቢያ ጉድጓድ የማዘጋጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡

የአረንጓዴ ልማት ማሕበር ፀሐፊ አቶ ስማቸው ፈንታሁን አነጋግረናቸው ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ የቆየ ሲሆን በዚህ አመት ደግሞ ማሕበሩ በ19 ወንድ በአንድ ሴት በጐ ፈቃደኞች በሆኑ በድምሩ 20 ሰዎች የተመሰረተ ሲሆን በየ ወሩ ከ40-150 ብር እያዋጣን ለሥራ ማስኬጃ እየተጠቀምን ቆይተን ከግብርና ከአካባቢ ጥበቃ የተለያዩ ባለሞያዎችን በመጠቀም ለዚህ ደርሰናል ብለውናል፡፡

## የማህበረሰቡን የጤና ችግር ለመፍታት የምርምር ሥራዎችን ወደ ማህበረሰቡ ማስረፅ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ

በታድዩ አስማረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመጀመሪያውን ሀገር አቀፍ የምርምር ጉባኤ ለሁለት ቀናት በዩኒቨርሲቲው ሰኔት አዳራሽ አካሂዷል፡ ፡ በጉባኤው ላይ አራት የማህበረሰቡ የጤና ችግሮች ናቸው ያሉቸውን በመውሰድ ምርምር እንዲካሄድባቸው በማድረግ የማህበረሰቡን የጤና ችግር ለመፍታት ኮሌጁ ጥረት እያደረገ ነው፡፡

የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር ጌታቸው ሙሉቀን የምርምር ጉባኤ ላይ ዩኒቨርሲቲያችን በአፍሪካ ውስጥ ምርጥ ከሚባሉ አስር የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን እየሠራ መሆኑን ጠቁመው ኮሌጁም የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ በመጋራት ለተግባራዊነቱ የተለያዩ የምርምር ሥራዎች እያካሄደ ይገኛል ብለዋል፡፡

የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የምርምርና ማህበረሰብ አስተባባሪ አቶ ገደፋው አበጀ የጉባኤውን ዓላማ ሲገልፁ በተመራማሪዎች የተሠሩ የምርምር ሥራዎች ሽልፍ ላይ ተቀምጠው ከሚቀሩ ወደ ማህበረሰቡ ሰርፀው እንዲገቡ በማድረግ የማህበረሰቡን የጤና ችግር ለመፍታት እንዲሁም ወጣት ተመራማሪዎች ከአንጋፋ ተመራማሪዎች ልምድ በመውሰድ ወደ ምርምር ሥራው እንዲገቡ ለማበረታታት ነው፡፡ በጉባኤው ላይ የተገኙ ፖሊሲ አውጭዎች እና ባለሙያዎች ያገኙትን የምርምር ውጤቶች ወደ ተግባር በመቀየር ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ ለመፍጠር እንዲያግዛቸው አቶ ገደፋው በተጨማሪ ገልፀዋል፡፡

በጉባኤው የቀረቡ የምርምር ሥራዎች በአራት ዘርፍ የተመደቡ ሲሆን እነሱም በተላላፊ በሽታዎች፣ በስርአተ ምግብ፣ በእናቶችና ህፃናት ጤና? እና የጤና አገልግሎት አሠጣጥ ችግሮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በጉባኤው ላይ የምርምር ውጤቶች 12ቱ በዩኒቨርሲቲው መምህራን የቀረቡ ሲሆን 8ቱ በተጋባዥ እንግዶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ የምርምር ሥራዎች ከማህበረሰብ ጤና ችግሮች ላይ በማተኮር ችግሩን ብቻ ሳይሆን መፍትሄም የቀረበ ሲሆን የማህበረሰቡን

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

## ፌዴሬሽኑን ለማጠናከር የሴት ምሁራን ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ተገለጸ

በሙሉጐጃም አንዱአለም

የአማራ ሴቶች ፌዴሬሽን ከክልሉ መንግስትና ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ታዋቂ ከሆኑ የክልሉ ተወላጅ ሴቶችና ሴት ዲያስፖራዎች ጋር የምክክር መድረክ አካሄደ፡፡

ፌዴሬሽኑ ህገ-መንግስቱ ያጐናፀፈውን የመደራጀት መብት በመጠቀም በክልሉ ውስጥ ያሉ ሴቶችን የክልሉ አማራ ሴቶች ማሕበር፣ የብ.አ.ዴ.ን ሴቶች ሊግ፣ የነጋዴ ሴቶች ማሕበር፣ የአካል ጉዳተኛ ሴቶች ማሕበር፣ የሴት ደራሲያን ማሕበርና የተመራጭ ሴቶች ፎረም በተሰኙ ስድስት ማሕበራት አደራጅቶ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት እየሰራ እንደሚገኝ የገለጹት የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ክብርት ወ/ሮ ትልቅሰው ይታያል ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም ከፌዴሬሽኑ ጋር አብሮ በመስራት ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የምክክር መድረኩን የከፈቱት የአማራ ክልል ምክር ቤት ም/አፈ ጉባኤ ወ/ሮ ወርቀዘብ ማሞ የውይይቱን ዋና ዓላማ ሲገልጹ ፌዴሬሽኑ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ላይ በግልፅ በመወያየት ጠንካራ ጎኖች እንዲቀጥሉና የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመለየት የአብሮነት ስሜት አስፈላጊ በመሆኑ መድረኩ ተዘጋጅቷል፡፡ ሴቶች በማሕበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ረገድ ያለባቸውን ተግዳሮቶች በመፍታት እንዲሁም አደረጃጀቶችን በማጠናከር በእውቀትም ሆነ በገንዘብ የሴቶችን ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ ወስዶ መስራት እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

በውይይቱ ላይ በኮትዲቯር የኢትዮጵያ አምባሳደርና የቀድሞ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የነበሩት ዶ/ር የሺመብራት መርሻ ውይይቱን ላዘጋጀው አካል ምስጋና አቅርበው ፌዴሬሽኑ ካቀፏቸው ማሕበራት በተጨማሪ የምሁራን ሴቶች እና የገበሬ ሴቶች ማሕበራትን በማካተት እየታየ ያለውን ጅምር ሥራ ማጠናከር እንደሚያስፈልግ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

My Reflection

# Code Switching as a classroom Discourse: Factional or Functional?

**Yenus Nurie (Department of English Language and Literature)**

In this paper, I am extremely passionate to share with you my ideas on the pedagogical implications of code switching in classrooms where diversified or multi-cultural societies like our students are attending. So as to help address the actual prospects of code-switching and its possible pedagogical effect on the overall personalities of students, the focus of my reflection is organized in the following ways. First, I will outline my beliefs and practical observations in some academic levels, which is immediately followed by my reflections on each experience to enliven my discussion.

I believe that teaching successfully is challenging, yet a rewarding job. I also believe that every student brings a wide range of prior knowledge, experience, reasoning, and interest to the classroom. Apart from this, I firmly believe that my students are different and are entitled to be involved in activities that engage them in their personal interests. Worded differently, as a teacher I must ensure if I could entertain all these differences as much as possible.

Given all the apparent advantages of switching codes to support teaching in the classroom where English is the medium of instruction, this paper takes the position that there is a fertile ground for effective teaching provided that teachers carefully employ translation at the right time. Thus, I am not intended to warn that translation must be rigidly eliminated in classrooms, but to suggest that we need to critically use native languages to foster teaching for a number of reasons. First, overuse use of translation may make students be bored with the lesson we teach. Second, wrong translation may give learners insufficient, confusing or even inaccurate information about the subject they learn. Third, as genuine teaching requires skills, translation in multilingual settings is apparently difficult.

**Recognizing that their English proficiency is limited, students will be interested in switching a code to participate actively in the actual classroom.**

To begin with, if properly used, code switching has positive consequences on students' learning. In fact, I don't completely ignore the positive effects of translation on the educational as well as psychological aspects of students' lives. For example, it is generally accepted that translation is an essential part of teaching and learning that can help teachers to foster teaching and enhance interpersonal communication with their students in the classroom, which in turn helps maintain to have good relationship among students. Naturally, it is also a desirable tool for teachers to diagnose their students' problems. Recognizing that their English proficiency is limited, students will be interested in switching a code to participate actively in the actual classroom. Code switching can also be considered in relation to ability and interest of learners, which no one can actually stop them if they wish to do in reality.

Taken together, however, these benefits of translation seem to carry less weight, and it is a far more complex phenomenon due to several pedagogical as well as pragmatic reasons. I personally argue that it might negatively affect the teaching learning process if it is not used appropriately. For example, students might lose interest in their learning as one of my friends told me five years ago; the teacher in his school used translation beyond a reasonable limit, and students were uninterested in the teacher's excessive translation into Amharic. As a result, he told me that all the students went to the school's principal and accused their English teacher by saying: "Why did you assign two Amharic teachers when we don't have any English teacher". From such practical reactions, one can infer that translation could be extremely dangerous not only in the pedagogies but also for the comfort of students.

Nevertheless, the major part of my argument is that translation is difficult if not impossible in multi-lingual classrooms where students come from various ethnic backgrounds. Imagine that you are teaching in a classroom where students coming from diversified ethnic backgrounds attending, which some of them only know their mother tongue. There is no doubt that no translation works in such kinds of settings. If we try to translate English into the most widely used language in the country, still we obviously get some students who use only their vernacular language, and have little or no knowledge of the language we translate into. Consequently, it can be painful for some students. In addition, even if we assume that our students can understand what we translate, they may interpret it differently, and in some cases, we may get our students' comprehension from bad to worse.

A few years ago, while I was offering a course in one of the colleges of our university, I was asked by a student for clarification. I tried to clarify my point using different techniques, but the student was still unable to grasp what I was doing. Finally, I decided to switch the code into Amharic, and as soon as I finished translating, students laughed out loud. When I asked why students laughed, a boy on the front desk told me that the student didn't know any language except his mother tongue, which I soon realized that I doubled the problem by shifting the medium and kept on clarifying the concept in English.

continue on page 10

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከሐምሌ ወር ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ

ባለፉት ተከታታይ እትሞች ተስፋሁን በገጠመው ችግር በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በስርቆት ወንጀል ተጥርጥሮ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ ምክንያት ግራው ገብቶት ኃሳቡ ሁሉ እየተመነዘረ አስቸግሮታል፡፡ ጓደኞቹም ቢሆኑ በደረሰበት ድንገተኛ ሁኔታ ስሜት ውስጥ ስለገቡ ከመጠየቅ ወደ ኋላ አላሉም፡፡ ይሁን እንጅ ከነገ ዛሬ እፈታለሁ የሚለው ተስፋ እየመነመነ ቢመጣም በጓደኞቹ ግፊት በቁጥጥር ሥር በዋለበት እስር ቤት ውስጥ ማንበቡን ቀጥሏል፡፡ ለመሆኑ ከአሁን በኋላ ምን ይገጥመው ይሆን? ቀጣዩን ማስታወሻ አብረን እናንብብ ………………………

> **ከውጭ አንድ ፖሊስ ጠራና ሌባው ሲቆጥረው የነበረውን ብር እያመለከተ ይህንን ገንዘብ በኤግዚቢትነት መዝግባችሁ አስቀምጡት በማለት ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ፤ ሌባውን ወደ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ እንዲወስዱት ትዕዛዝ ሰጠ፡፡**

በፖሊስ ጣቢያው ሌቦች አንድ፣ አንድ እያሉ ቀስ በቀስ እየተያዙ እየገቡ ነው፡፡ “አሁኑኑ ኢንስፔክተሩን አነጋግርለት” ሲለው ሣጅን “እሽ!” ብሎ ወደ ቢሮው በመሄድ ለረጅም ሰዓታት አብሮት ቆየና በመጨረሻ እኔን አስጠራኝ፡፡

ተጠርቼ እንደገባሁ ኢንስፔክተሩ ስሜን ጠራና “ታዲያስ! ማረፊያ ቤት እንዴት ነው? መቼም አንዳንዴ ወንጀል ሲፈፀም ጉዳዩን ለመከታተልና ለማጣራት ሲባል በወንጀሉ ዙሪያ ያልነበሩ ሰዎች መንገላታት አልፎ፣ አልፎ ይከሰታል፡፡ ስለዚህ አንተም ጉዳዩን ለማጣራት ሲባል ሰሞኑን እዚህ የቆየኸው ከዚህ አኳያ መሆኑን መገንዘብ አለብህ፡፡ ደግሞ እኮ አንተ እዚህ ባትሆን ኖሮ የዚችን ካርድ አድራሻ አናገኛትም ነበር፡፡ ያው እንደሚታወቀው ሁሉ ወንጀለኞች እዚህም ከገቡ በኋላ በተስፋ መቁረጥና በማን አለብኝነት በቁጥጥር ሥር ላይ ሆነውም እንኳን ወንጀልን ከመሥራት አይቆጠቡም፡፡ ለዚህም ነው ሣይፈራ ሣይቸር የሰውን መታወቂያ ካርድ እሥር ቤት ላይ ለገበያ ያቀረበው፡፡ ብቻ ካርዱን ክትትል በማድረግ በእጁ ያስገባውን ሰው ልታደንቀው ይገባል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ይህ ካርድ ከእዚህ እሥር ቤት እንዲወጣ ይደረግና ሌላ ወንጀል ሊሠራበት ይችል ነበር፡፡” በተቀመጠበት ተሽከርካሪ ወንበር ወደ ኋላ እንደ መዝናናት ካለ በኋላ “መቼም እንግዲህ ስንፈልግህ የምትመጣ ሆኖ ከተጠረጠርክበት ወንጀል ነፃ ስለሆንክ ከዚህ ወጥተህ በሰላም ትምህርትህን በመከታተል ለጥሩ ውጤት እንድትበቃ እመኝልሃለሁ” በማለት አሰናበተኝ፡፡ ሣጅንም ሁኔታውን ሲያዳምጥ ቆይቶ “እንግዲህ ስላደረጋችሁት ክትትልና ውጤት በጣም እያመሰገንን በእውነቱ ጎጂ ከዚህ ቀደምም ሌባ አድኖ በመያዝ የሠራው ጀብዱ ስለነበር ዋና ተባባሪያችሁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመናገር እፈልጋለሁ” አለና ምኝታ ቤት ላይ ስለያዝኩት ሌባ ታሪክ በዝርዝር ነገረው፡፡ ኢንስፔክተሩም “እንዴ! እንዴ! ይህንንስ አላወቅሁም ነበር ካለ በኋላ በል እንግዲህ ለወደፊቱ በፖሊስ ላይ ቂም እንዳትይዝ” በማለት ሲጨብጠኝ “መታወቂያዬ አይሰጠኝም?” አልኩት፡፡ መርማሪውም “ይሰጥሃል፡፡ ነገር ግን አሁን ለያዝነው የምርመራ ተግባር ስለምንፈልገው እኛ ዘንድ መቆየት አለበት፡፡ ይሁን እንጅ ግቢ ውስጥ እንዳትቸገር ከእኛ ዘንድ መኖሩን የሚገልፅ ማስረጃ እንጽፍልሃለን” አለና ወዲያው በሌባ መሠረቁንና በፖሊስ እጅ የሚገኝ መሆኑን የሚገልፅ ሀሳብ በመጻፍ ማህተም አድርጎ ሰጠኝ፡፡

እኔም ከእሥር በመለቀቄ ደስ ብሎኝ ፖሊሱንና አብሮኝ የሚበላውን መቋርሰኛዬን ተሰናብቼ ጓዜን በመጠቅለል ጉዞ ጀመርን፡፡ ትንሽ ከተጓዝን በኋላ ሣጅንን ለሻሼ ስልክ እንዲደውልላት ጠየቅኩት፡፡ እሱም ደወለልኝ፡፡ በተደወለላት ከግማሽ ሰዓት በኋላ ከአንድ ካፌ ሻይ ቡና እያልን ጠበቅናት፡፡ ተፈትቼ በማየቷ በጣም ደስ አላት፡፡

ከዚያም ስናወራ ቆይተን አንድ ሆቴል ውስጥ በመግባት ራት በላን፡፡ ራት ከበላን በኋላ ሳጅንና ሻሼ እኔ ልክፈል እኔ ልክፈል ግር ግር ፈጠሩ፡፡ ነገር ግን ሻሼ መቼም ከተማሪ እኔ ሳልሻል አልቀርም በማለት በኃሳብ አሸነፈችና ከፈለች፡፡ ሣጅን ለእኔ ምግብ ሲያመጣበት የነበረውን ሣህን ለባለቤቶች አመስግኖ ሲመልስላቸው ሻሼ ደግሞ የራሷን ሣህን በመያዝ ተሰናብታን ሄደች፡፡ ከዚያም ብርድ ልብሴንና አንሶላዬን እንደዚሁም ከፕላስቲክ የተሠራውን ምንጣፌን ሰብስበን በመያዝ ወደ ግቢ አመራን፡፡ ግቢ ስንደርስ የምኝታ ቤት ጓደኞቼ በደስታ ተቀበሉኝ፡፡ ከዚያም በተማሪዎች መዝናኛ ሻይ ቡና በማለት ወደ መኝታ ቤት ከተመለስን በኋላ ስለመሰንበቻዬ አንድ ባንድ ተረኩላቸው፡፡ ሁሉም ዝም ብለው ሲያዳምጡኝ ቆዩና ከመካከላቸው ቀልደኛው ጓደኛችን “ጎዴ እንዲህ በአጭር ጊዜ ተደጋጋሚ ታሪክ ስትሠሪ እኔ ምንም ታሪክ ባለማስመዝገቤ እየቆጨኝ ስለመጣ በቃ ነገውኑ እሸፍታለሁ” ሲል ሌላው ቀበል አደረገና “የት ነው የምትሸፍተው?” ሲለው “ያው! መቸስ ግፋ ቢል ሳይበራሪ ሊሆን ይችላል፡፡” በማለት ትንሽ ፈገግ አደረገን፡፡ እየመሸ በመምጣቱም የተወሰኑት ጓደኞቼ ሲተኙ የተወሰኑት ደግሞ ወደ ሳይበራሪ ሄዱ፡፡

እኔም እናቴ ይህንን ጉድ ሳትሰማ ከእሥር ቤት በሰላም በመፈታቴ ታላቅ ልባዊ ደስታ እየተሰማኝ ፈጣሪዬን አመስግኜ የሰላም እንቅልፍ ተኝቼ አደርኩ፡፡ ነገር ግን የሔርሜላ ናፍቆት አዕምሮዬን እየበጠበጠኝ ይገኛል፡፡ ችግሩን እንዴት ማቃለል እንደምችል ግራው ገብቶኛል፡፡ ይህን በተመለከተ የማልመው የማቅደው ነገር ሁሉ በቀላሉ ሲናድብኝ ተስፋ ልቆርጥ እልና የእናቴን ሁኔታ ሳስበውና ትምህርቴን በደንብ መከታተል እንዳለብኝ ስወስን እንደገና ተመልሶ ሔርሜላን የመፈለጉን ሁኔታ እንድቀጥልበት የሚገፋፋኝ ኃይል ይመጣብኛል፡፡

ከእስር ቤት ከተፈታሁ በነጋው ጠዋት በመታወቂያዬ ፋንታ ፖሊሱ የሰጠኝን ማስረጃ በመያዝ ወደ ግቢው ፖስታ ቤት በመሄድ ፖስተኛው ደብዳቤዬን እንዲሰጠኝ ስጠይቀው ዛሬም መታወቂያ ጠየቀኝ፡፡ ፖሊስ የሰጠኝን ማስረጃ ስሰጠው ደግሞ “ይሄ ምን የሚሉት ነው?” በማለት በጥያቄ አፋጠጠኝ፡፡ ከመናደዴ የተነሣ ‹‹ማንበብ አትችልም? እኔ የፃፍኩት እንዳይመስልህ›› አልሁት፡፡ እሱም በፈንታው በመቆጣት “ይህ የማንበብ ወይም ያለማንበብ ጉዳይ አይደለም፡፡ በስህተት አንዱ የሌላውን ደብዳቤ እንዳይውስድ የሚደረግ ጥንቃቄ እንጂ” አለና ማስረጃውን እንደገና በትኩረት ሲመለከታት ቆየና ቀና ሲል “ባለፈው መታወቂያዬ ስለጠፋብኝ እባክህ ስጠኝ ስልህ ምንም መልስ ሳትሰጠኝ በከንቱ ተጉላልቼ ስሄድ ይባስ ብሎ ለሌላ ችግር ተዳርጌ ሰነበትኩ፡፡ ደብዳቤውም ምን እንደሚል ሳላውቀው ይኸውና ያለምክንያት ተቀምጦ ሰነበተ” ስለው አንገቱን አወዛወዘና ከመደርደሪያው በፊደል ተራ ከተቀመጡት ደብዳቤዎች መካከል ሁለት ፖስታዎች በማንሣት በሆነ መዝገብ ላይ አስፈረመና ሰጠኝ፡፡ የደብዳቤዎቹን አድራሻ ስመለከት አንደኛው ከእናቴ ሲሆን ሁለተኛው ሐዋሳ ከሚገኘው ጓደኛዬ የተላኩ ናቸው፡፡ በመቻኮል ቅድሚያ በመስጠት የእናቴን ደብዳቤ ከፈትኩት፡፡ እንዲህ ይላል…………..

ለውድ ልጄ ተስፋሁን ቦጋለ ለጤናህ እንደምን አለህልኝ? ትምህርትስ እንዴት ነው? ይህንን ደብዳቤ የፃፍኩልህ በአጋጣሚ ደብረ ማርቆስ ዘመድ ለመጠየቅ በሄድኩበት ጊዜ ነው፡፡ ደብረ ማርቆስ ብዙ ተለውጣለች፡፡ ቀደም ሲል ከእኔ ጋር አብረው ይማሩ የነበሩት ጓደኞቼ የተወሰኑት የዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው ሳያቸው ወደ ኋላ ተመልሼ ማሰብ ስጀምር ቆጨኝ፡፡ ያን ጊዜ ትምህርቴን ባላቋርጥ ኖሮ የእኔ እጣ ፈንታም እንደነሱ ይሆን ነበር፤ ግን መቼስ እጣ ፈንታ ሆነና ገበሬ ሆኜ ቀረሁ፡፡ በዚህም የተነሣ ብቻዬን ብዙ አወጣሁ አወረድኩ፡፡ እርግጥ ነው፡፡ ምንም እንኳን እኔ ባቋርጥም የማህፀኔ ውጤት የሆንኸውን አንተን በማስተማሬና ለዚህ ደረጃ በማድረሴ ደስ ቢለኝም የበለጠ ደግሞ አሁን እኔም ለመማር ልቤ ተነሳስቷል፡፡

በመሆኑም እዚህ ደብረ ማርቆስ በመጣሁበት እግረ-መንገዴን ዞን ትምህርት መምሪያ በመሄድ ትምህርቴን እንዴት መቀጠል እንዳለብኝ ስጠይቃቸው በአዲሱ የትምህርት ካሪኩለም መጀመር ያለብኝ ዘጠነኛ ክፍል እንደሆነ ነገሩኝ፡፡ በዚህም መሠረት የስምንተኛ መልቀቂያ ፈተና ውጤቴንና ከዘጠኝ ወደ አስር ያለፍኩበትን ሰርተፍኬት ከደብረ ማርቆስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አውጥቼዋለሁ፡፡ ሌላው አንተ ወደ ባሕር ዳር ከሄድክ በኋላ የአካባቢው ወንዶች በተለያዩ መንገድ በሴትነቴ እየተፈታተኑኝ ስለሆነ ከአልታሰበ ችግር ከመውደቄ በፊት ደብረ ኤልያስ ወይም አማኑኤል ከተማ ቤት ተከራይቼ ትምህርት ለመጀመር አስቤያለሁ፡፡ ያለኝ ኃብትና ንብረት ለአንተና ለእኔ መማሪያ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ ደግሞ ብዙ መሬት ስላለን ያንን እያሳረስን ብንጠቀም አይቸግረንም፡፡ ዘንድሮም ከመቶ ሃያ አምስት ኩንታል ያላነሰ ስንዴ ስላስመረትኩ በደህና ብር ሸጬዋለሁ፡፡ ሌላው ቦቆሎው፣ በርበሬው እና ሌሎችም የሰብል ዓይነቶች ምርት ባማረ ሁኔታ ሰብስቤያለሁ፡፡ ከብቶችንም ቢሆን ለመሸጥ እያሰብኩ ነው፡፡ ብቻ ለሁሉም በጋራ ተገናኝተን እንመካከራለን፡፡

ተስፋሁን ባለፈው ስሸኝህ ብዙ ነገር አያስፈልገኝም በማለትህ በቂ ገንዘብ አልሰጠሁህም ነበር፡፡ አሁን ግን ነገሩን ወደ ኋላ ተመልሼ ሳስበው አንተም እኔም ተሳስተናል ቢያንስ ያኤ የሞባይል ስልክ መግዣ ጨምሬ መስጠት ነበረብኝ፡፡ አሁንም ለአንዳንድ ነገሮች

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የኔ ሃሳብ

# የመሪነት ብቃት ለራዕይ 2017 ስኬት

አለባቸው አስፋው (ከቢዝነስና ኢኮኖሚክስ)

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በቀጣይ ጥቂት ዓመታት ውስጥ በአፍሪካ ካሉት ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ አስቀምጦ በመስራት ላይ የሚገኝ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ይህን ራዕይ በማሳካት ረገድ ቁልፍ ተጽዕኖ ካላቸው ጉዳዮች አንዱ በሆነው የአመራር አጀንዳ ላይ የቻሉትን ያህል ማለት ተገቢ በመሆኑ ይህን መነሻ አቅርቤያለሁ። በምጽፋቸው ጽሁፎች ውስጥ ከትምህርትና ንባብ፣ ከተግባር ስምሪት እና ከዕለት ዕለት ገጠመኝ በመነሳት መነሻዎችን ሳቀርብ አንባቢዎች ራሳቸውን አሁን ካሉበት ሁኔታ ጋር አጣጥመው በማየት አስተያየታቸውን እንዲለግሱ በትህትና እጠይቃለሁ። በተቻለኝ መጠን ጽሁፎቹ ጥቅል ሆነው አንባቢው ራሱንና ያለበትን ተቋም በዚያ ውስጥ ሆኖ እንዲያይ ለማድረግ እሞክራለሁ። ጽሁፉ አላግባብ እንዳይረዝም በአንዱ ፆታ የተገለጸው ለሁለቱም እንደሚሰራ ቢታይልኝ።

መሪ መሆን ከሠው ጋር መስራትና ግብ ማሳካትን የሚይዝ እኛነት ነው። መሪ የሚባለውም በስልጣኑ ወሰን ውስጥ ከተካተቱ ህጎች ባሻገር በግለሰብነቱ የሚኖረው ተጽዕኖ ፈጣሪነት ላይ የሚያርፍ ጉዳይ ነው። እናም የዘመኑ የመሪነት ትርጉም በወሳኝነት ከተጽዕኖ ፈጣሪነት ጋር የሚያያዝ ነው። ስለመምራት ስናስብ መሪን፣ ተከታይን፣ ተግባቦትንና ሁኔታን አስተሳስረን በመመዘን ይሆናል። እንዚህን ተገንዝቦ ውጤትን ማዕከል በማድረግ አዋህዶ ስኬት የሚያመጣው ሰው ተጽዕኖ ፈጣሪ ሆኗል እንላለን። መሪነት አገልጋይነትም ነው። በግል ድርጅታችንም ሆነ ለሌሎች ተቀጥረን በምንሰራበት ዘርፍ ሌሎችን አስከትለን ለውጤት የምንተጋ ከሆነ እያገለገልን ነው ማለት አይደለምን?

መምራት ከያዝነው ወንበር ጋር ብቻ የተያያዘ ከሆነ ሥራን የምናሰራው በትዕዛዝና ወረቀት ላይ ባሉት ህጎች ብቻ ተመስርተን ነው ማለት ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ሠዎች ያላቸውን አቅም አሟጠው በመጠቀም ሥራ ላይ ያውላሉ ማለት አይቻልም። ለምን ካልን መሪዎቻቸው ያንን ያደርጉ ዘንድ አወንታዊ ተጽዕኖ አላሳረፉባቸውምና ነው። ተቋማዊ ስኬት ደግሞ ውስጡ ለውጤት የሚንቀለቀል ፍላጎት ያለው ሠራተኛ ካልተፈጠረ የሚሳካ አይሆንም።

ሠዎች መሪነት በተሰጠ ስልጣን ከፍታ ልክ እንደሚመዘን ሲገምቱ ይስተዋላል። ነገር ግን ያ ላይ ጉብ ያለው ሰው ዕውን ተጽዕኖው ታች ድረስ ይሰማልን? ብለን ስንጠይቅ እያለ የሌለ ብዙ መሪ ተብዬ ልናገኝ እንችላለን። እስቲ እርስዎ ከራስዎ ውጭ እንድ ሰው በስርዎ የሚያሰራ ከሆነ እርስዎ ባይኖሩ ባሉበት የሥራ ዘርፍ ውስጥ ሳይሰራ የሚያድር የሚውለውን፣ በተቋሙ ላይ የሚፈጠረውን እንከን፣ በአገር ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማስላት ይሞክሩ። ባይኖሩም ችግር የለውም ይሆን? እንግዲያው ትርፍ አንጀት ሳይሆኑ አይቀርምና አስተዋጽኦ እንዲኖርዎ መላ ይፈልጉ።

እናም መሪነታችን ባለን ተጽዕኖ የማሳረፍ ልክ እንጂ የተቀመጥንበት የስልጣን ቆጥ አይሆንም። እና በስልጣን ዕርከን ከሰማይ ጥቂት ዝቅ ብሎ የተቀመጠው ሰው ተጽዕኖ ፈጣሪ መሪ ካልሆነ መሪ አይደለም ማለትህ ነው ከተባልኩ መልሴ ወፍራም አዎ ነው። በግንባር ሰውየው መኖሩን እያዩ ተፍ ተፍ የሚሉ አጃቢዎች በሌለ ቀን ተኝተው የሚያናኮራፉ አሊያም በራሳቸው ጉዳይ ታጥረው ሲተሙ የሚታይ ከሆነ ያ ሰው እንዴት መሪ ተብሎ ሊነሳ ይቻላል - ካቦ እንጂ። በፕላኒግ ዘርፍ ዳታ መሰብሰብ፣ መተንተንና መረጃ ማመንጨት፣ መነሻ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የቀረቡ ዕቅዶችንና የሪፖርት ሰነዶችን መርምሮ ግብረ መልስ መስጠት መደበኛ የዘርፉ ተግባር ሊሆን ይችላል። ይህም የዘርፉ ሠራተኞች የሥራ ዝርዝራቸው ተለይቶ ተሰጥቷቸው ተግባሩን በሚመሩላቸው ደብዳቤዎች መነሻነት ሊፈጽሙት ይችላሉ። ግን እነዚህ ተግባራት ደብዳቤውን የሚመራው አለቃ በሌለበት ጊዜስ ይከናወናሉ ወይ ነው ጥያቄው። ከልምድ እንደምናየው ብዙዎቹ የመንግስት ተቋማት አለቆች ከተጓደሉ ሥራ የሚቆምባቸው ናቸው። ደብዳቤ የሚመራና ትዕዛዝ የሚሰጥ አለቃ በሌለበት ጌዜ ፈቃድ ሳያስፈልግ ሥራን መዝጋት የሚቻልበት ገጠመኝ አድርጎ መውሰድ የተለመደ ተግባር ነው። ደብዳቤዎችን መመራራት ጤናማ የቢሮክራሲ ሂደት ነው። የጀርመኑ ማክስ ዌበር ቢሮክራሲ ተግባራትን ወጥነት ባለው አግባብ፣ በቅልጥፍናና አምክኗዊ በሆነ አስተሳሰብ ለመፈጸም የሚያስችል ስርዓት መረጋገጫ መሳሪያ እንደሆነ ያስረዳል። በዚህም ምክንያት መነሻው ለመንግስት አስተዳደር ቢሆንም እየቆየ ግን ከመንግስት አልፎ ትላልቅ የንግድና የረድኤት ድርጅቶችም የሚመሩበት ብልሃት ሊሆን ችሏል። የአውሮፓ መነሻ እንዳለውና እየዳበረ መጥቶ ለአለም ብልጽግና አስተዋጽኦ እንዳበረከተ የሚነገርለት ቢሮክራሲ በኛ ዘንድ ስራን ማሳለጫ ሳይሆን ለቅልጥፍና ማሰሪያ ግዝት ሆኖ አለቃ ሊያየው የሚገባውንም የማይገባውንም ሰብስቦ በአንድ ቧንቧ እንዲሾልክ በማስገደድ ለደከመ አፈጻጸም መንስኤ ሲሆን ኖሯል። በዚህም ምክንያት አለቆችና ሠራተኞች የሚመለከታቸውን ተግባር በበለጠ ለመፈጸም የሚጠቀሙበትን ያህል ከሥራ ፋታ ለማግኘትና ለመሸሽም የሚጠቀሙበት እንዳሉ ከዕለት ዕለት መስተጋብር ተነስቶ መመስከር ይቻላል።

በእርግጥም መሪ ባለበትና በተፈጠረበት የሥራ ከፍል ፎርማሊቲ ሠራተኛን ተግባርን ከመፈጸም አይገድበውም። ሥራዎች ታዘዙም አልታዘዙም በቅደም ተከተላቸውና በአስፈላጊነታቸው ተመስርቶ ይከናወናሉ። ይህ በሌለበት ደግሞ "ኃላፊው አልመራውም" በሚል ተግባር ተንጠልጥሎ ሳይከናወን ያድራል፤ ይውላል፤ ኸረ ይከርማል። ኃላፊው ሲመራው ስራው "ሀ" ተብሎ ይጀመራል። በነገራችን ላይ ሥራው ውሎ እንደሚያድረው ሁሉ ይህን ተግባር ሊፈጽም የሚገባው ሠራተኛም ያለ ሥራ ጦሙን ውሎ ጦሙን ያድራል። አንድም አለዕውቀት አሊያም በስንፈትና ልግመኝነት። ታዲያ ማን አተረፈ? ካልን መልሱ ማንም ነው። እንዲያውም ኪሳራ ይኖርብናል እንደተቋም፣ እንደሠራተኛ።

> ከልምድ እንደምናየው ብዙዎቹ የመንግስት ተቋማት አለቆች ከተጓደሉ ሥራ የሚቆምባቸው ናቸው። ደብዳቤ የሚመራና ትዕዛዝ የሚሰጥ አለቃ በሌለበት ጊዜ ፈቃድ ሳያስፈልግ ሥራን መዝጋት የሚቻልበት ገጠመኝ አድርጎ መውሰድ የተለመደ ተግባር ነው።

ዕውቁ ንግግር አዋቂና የአመራር ጠቢብ ጆን ማክስዌል መሪነትን በአምስት የተለያየ የዕድገት ደረጃ ከፋፍሎ ያቀረበበት ሁኔታ ራስን በተለይ እንደመሪ ለመፈተሽ የሚያስችል መስሎ ስለተሰማኝ በአጭሩ የራሴን ዕይታ አክዬ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ።

### አንደኛ ደረጃ አመራር፡ በወንበር(ስልጣን) መምራት

በዚህ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሪዎች ስልጣንና ስልጣናቸው የሚሰጣቸውን የማዘዝ መብት ብቻ እየተጠቀሙ ሥራንና ሠራተኛን ለማዋሃድ የሚተጉ አለቆች ናቸው። እናም እነዚህ ሰዎች የወንበር ጌቶች ናቸው ሊባሉ ይችላሉ። ምክንያቱም ያችን ወንበር ከለቀቁ የሚያያቸውም ሆነ የሚያስታውሳቸው የለም፣ እነሱም በተጨባጭ በወንበሯ ላይ እያሉ ሠራነው ብለው የሚያስታውሱት እምብዛም ነው። ዋናው የሥራ መስሪያና ማሰሪያ ቁልፋቸው የተቀመጡበት የሥልጣን ደረጃ ነው። ግርማ ሞገሳቸው የሚመነጨው ከሥልጣናቸው በመሆኑ ያ በጎደለ ቀን ከተራው ህዝብ ጋር ለመመሳሰል ጭምር ጊዜ ሊወስድባቸው ይችላል። ሥራን የሚያሰሩት የያዙት ወንበር የሚያስገኘውን የማዘዝ መብት(ስልጣን) ተጠቅመው ነው።

ማንም ጀማሪ አለቃ ከዚህ ደረጃ መጀመሩ የሚጠበቅ ነው። አንዳንዶቻችን ተቋሙን እንኳ በአግባቡ ሳናውቀው በሁለት መስመር ደብዳቤ የ--- ቡድን መሪ/አስተባባሪ ወይም ኃላፊ የሚል የሥራ ክፍል ኃላፊነት ሊደርሰን ይችላል። እናም የመማር ፍጥነታችን እንደተጠበቀ ሆኖ መጀመሪያ ላይ የምትኖረን ማዘዣ ያችው በቀላጤዋ የተገኘችው ስልጣን ብትሆንም ከማግስቱ ጀምሮ ክፍሉን በተገቢው ሁኔታ የምንመራው ሆኖ ይሰማናል። እርግጥ ነው እናዛለን፣ ይሁንታችን ይጠየቃል። ምክንያቱ ደግሞ ደመወዝ ይፈልጋሉ፣ ማደግ ይሻሉ፣ ለበላይ መታዘዝም ተገቢ ነው። እርግጠኛ መሆን የሚቻለው ግን በዚህ ደረጃ ያለ ኃላፊ ከባልደረቦቹና ከበታቾቹ የሚያገኘው አገልግሎት የችሎታቸውን እጅግ ያነሰ መጠን መሆኑን ነው። ምክንያቱም የሚሰሩት በስልጣኑ ሊያስከትልባቸው የሚችለውን ጫና ለማምለጥ ብቻ በመሆኑ ነው። በዚህ ደረጃ ውስጥ ባለ ኃላፊ ሥር የሚሰሩ ሠራተኞች ጧት ሲገቡ ጀነን ኮራ ብለው ነገር ግን የሰዓት ፊርማ እንዳታመልጣቸው አድርገው ሲሆን ሲወጡ ደግሞ ቅድመ ዝግጅቱን ግማሽ ሰዓት አስቀድመው የሚጀምሩና ራሳቸውን የሚያበጃጁ ለዕለቱ የወጡትን ስለመከወኑ የማያሳስባቸው፣ የጀመሩትን ሳያትቡ ውልቅ የሚሉ ናቸው። እናም ደረጃ አንድ ላይ ያለ

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

## እንግዳችን

# የዘመን አቆጣጠር እንዴት እንደሚቀመር ልብ ብለው ያውቃሉ?

**የዚህ ወር እንግዳችን በዩኒቨርሲቲያችን የዐባይ ባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማእከል ዳይሬክተርና የግእዝ መምህር ናቸው፡፡ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር አስመልክቶ ከናይል ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ቃለ መጠይቁን እነሆ፡፡ መልካም ንባብ!**



ናይል፡ በመጀመሪያ ስምዎንና የሥራ ኀላፊነትዎን ቢያስተዋውቁን?

ዶ/ር ሙሉቀን፡ ስሜ ሙሉቀን አንዱዓለም እባላለሁ፡፡ ሥራዬም የዐባይ ባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማእከል ዳይሬክተርና የግእዝ መምህር ነኝ፡፡

ናይል፡ ዐባይ የባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማእከል መቼ ተመሠረተ?

ዶ/ር ሙሉቀን፡ ዐባይ የባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማእከል የተመሠረተው በ2004 ዓ.ም ነው፡፡

ናይል፡ ዓላማዉ ምን እንደሆነ ሊነግሩን ይችላሉ?

ዶ/ር ሙሉቀን፡ አወ እችላለሁ፡፡ ማእከሉ የተመሠረተበት ዋና ዓላማ ሀገር በቀል ዕውቀትን በማፈላለግ፣ እንዴት እንደተመሠረተ፣ በምን ዓይነት ሁኔታ እንዳለ፣ ወደፊትስ እንዴት መቀጠል እንዳለበት ለማጥናት፣ ለመመራመርና ለማልማት እንዲሁም ለማሳደግ ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- እናት አገራችን ኢትዮጵያ ታሪካዊት ሀገር ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በተለያየ ዘርፍ ያለ ሀገር በቀል ዕውቀቷ በአግባቡና በተጠናከረ መልኩ ተጠንቶ ፖለቲካዊ፣ ማኅባራዊና ኢኮኖሚያዊ ግብአትን ለማግኘት፣
- በተጨማሪም የሌሎች ሀገሮችን የባህል ጠቀሜታና ተሞክሮ ብቻ ወደኛ ማምጣት ሳይሆን የእኛንም ባህል አጥንተን የምናገኘውን ውጤት ከእኛ አልፎ ለሌሎችም በማስተላለፍ ሀገራችን የዕውቀቱ ፈጣሪ መሆኗን ለማሳየት፣
- ሀገራችን ኢትዮጵያ የታሪክ መዛግብት ሲዳሰሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንደነበረችና ከታላላቅ ሀገሮች አንዷ እንደነበረች በሰፊው ያስረዳሉ፡፡ ያ ምሥጢር ምን እንደ ነበረ ተመራምሮና ራስን ፈትሾ ትውልድ ያላወቀውን እውነታ ለማሳወቅና የትላንት ታሪክዋ ለዛሬ አስተማሪ ስለሆነ ይንን ማጥናት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ የተመሠረተበት ዓላማ ይህን ይመስላል፡፡

ናይል፡ ማእከሉ በአሁኑ ሰዓት የሚሠራቸውን ሥራዎች በዝርዝር ቢነግሩን?

ዶ/ር ሙሉቀን፡ ምንም እንኳን ማእከሉ በ2004 ዓ.ም ተመሠረተ ቢባልም ቅሉ ወደ ዋና ሥራው በመግባት እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ የተሟላ የጥናትና ምርምር ሥራ ተሠራ ብሎ መናገር አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም ማእከሉ ለራሱ የሆነ ቢሮ አልነበረውም፣ በራሱ በጀት የጥናትና ምርምር ሥራዎች አልተካሄዱም፡፡ በእርግጥ ዳይሬክተር ተመድቦለት መለስተኛ ሥልጠናዎች፣ ዐውደ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ሌሎችም መሰል ጉዳዮች ተከናውነዋል፡፡ በመሆኑም እነዚያ ሥራዎች ለአሁኑ የጥናትና ምርምር ሥራ መሠረቶች በመሆናቸው ያበረከቱት አስተወጽኦ ቀላል አይደለም፡፡ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ግን የራሱ በጀት ተመድቦለት፤ ቢሮ ተሰጥቶት፤ የጥናትና ምርምር ቡድን ተዘግጅቶለት የተለያዩ ዐውደ ጥናቶችን በሀገር አቀፍም ሆነ ዓለም አቀፍ ደረጃ እስከ ማዘጋጀት የደረሰበት ሁኔታ አለ፡፡ ባለፈው ዓመት በሀገር በቀል ዕውቀት ላይ ጥናትና ምርምር ሲካሄድባቸው የቆዩና አሁንም የቀጠሉ አራት ፕሮጀክቶች አሉ፡፡ በ2008 ዓ.ም ደግሞ ሌሎች አምስት ፕሮጀክቶች በውድድር ተመርጠዋል፡፡ በአጠቃላይ በ2008 ዓ.ም ካለፉት ጋር ሲደመሩ ዘጠኝ ፕሮጀክቶች በማእከሉ በጀት እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡ ሌላው ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ማእከላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ላይ እንገኛለን፡፡ ለዚህም እነሀምቡርግ ዩኒቨርሰቲዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የማኅበረሰብ አገልግሎት ማለት በዋናነት ሕዝብን ማገልገል እና ማስተማር ነው፡፡ በዚህም መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም በጀርመን፣ በኢትዮጵያ፣ በኤፍ ኤምና በአማራ ሬዲዮዎች፣ በኢትዮጵያ TV፣ በአማራ TV፣ በሪፖርተርና በናይል ጋዜጣ፣ እኔም የማእከሉ አባላትም በተደጋጋሚ ጊዜ የማእከሉን፣ የዩኒቨርሲቲውንና የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ለማሳወቅና ለማስተማር ሞክረናል፡፡ ወደፊትም እንቀጥልበታለን፡፡ በተጨማሪም የዳበረና የተካበተ ልምድና ተመክሮ ያላቸው ዕውቅ ምሁራንን በመጋበዝ፣ ሕዝባዊ ትምህርት (ፐብሊክ ሌክቸር) እንዲካሄድ አድርገናል ወደፊትም ይቀጥላል፡፡

ናይል፡ በእኛና በአውሮፓ የዘመን አቆጣጠር መካከል ያለውን ልዩነት ሊነግሩኝ ይችላሉ?

ዶ/ር ሙሉቀን፡ በአውሮፓ የዘመን አቆጣጠርና በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ከመናገሬ በፊት አጠቃላይ የሆነ ነገር ላስቀድም፡፡ ብዙ ሰው እንደሚመስለው የዘመን አቆጣጠር የእኛና የአውሮፓ ብቻ ይመስለዋል፡፡ ግን በዓለም ላይ ከ33 በላይ የሚሆኑ የዘመን አቆጣሮች አሉ፡፡

በዚህም መሠረት እያንዳንዱ የተመሠረተበት ጊዜ፣ የሚጠቀመው ዘዴና ቀመር የተለያየ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሁሉም ዓላማ መንፈሳዊ ይዘትም ዓለማዊ ይዘትም አለው፡፡ ነገር ግን መነሻዎቹ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ፀሐይና ጨረቃ በተናጠልም በመደመርም ነው፡፡ ወደ ክርስቲያኑ ጎራ ብመለስ መንፈሳዊ ይዘቶቹ ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1ኛ. ለአዳም የተሰጠው የተስፋ ቃል እና

2ኛ. ኀልፈተ ዓለም (በ8ኛዉ ሺህ የዓለም መጨረሻ ይሆናል) ፡፡ የሚለው

⇨

# እንግዳችን ...

Gregorian calendar፡

**Ethnic and national**

[+] Chinese calendars

- *Assyrian calendar*
- *Bengali calendar*
- *Berber calendar*
- *Bikram Samwat*
- *Chinese calendar*
- *Chinese calendar*
- *Chinese constellation*
- *Ethiopian calendar*
- *Hebrew calendar*
- *Icelandic calendar*
- *Indian national calendar*
- *Iranian calendar*
- *Irish calendar*
- *Islamic calendar*
- *Javanese calendar*
- *Korean calendar*
- *Lithuanian calendar*
- *Mesoamerican calendar*
- *Swedish calendar*
- *Thai calendar*
- *Thai lunar calendar*
- *Thai solar calendar*

**Liturgical**

- *Bahá'í calendar*
- *Buddhist calendar*
- *Coptic calendar*
- *Dominical letter*
- *Ethiopian calendar*
- *Filianic calendar*
- *Hebrew calendar*
- *Islamic calendar*
- *Julian calendar*
- *Revised Julian calendar*
- *Tabot Calendar*
- *Tabular Islamic calendar*
- *Zoroastrian calendar*

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ናቸው፡፡ እስኪ ባጭሩ እንመልከታቸው፡፡

1ኛ. የአዳም ተስፋ፡- የሰው ልጆች ሁሉ አባት የኾነው አዳም ከስሕተቱ ተመልሶ ፈጣሪዉን ይቅርታ በጠየቀበት ሰዓት እግዚአብሔር አምላክ "ከ5 ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንህአለሁ" ብሎ የተስፋ ቃል ኪዳን ሰጠው፡፡ 5 ቀን ተኩል (5.5) ማለት 5500 ዘመን ማለት ነው፡፡ ይህም በሃይማኖት አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ሺህ ቀን ነው ይላል ነቢዩ ዳዊት (5.5 × 1000 = 5500) ፡፡ በዚህ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶና አድጎ በ30 ዘመኑ በስቅላት ሞቶ እንደሚያድነው አስቀድሞ ስለተናገረ የመጀመሪያው ምክንያት ያንን የድኅነት ቀን ለማወቅ የተደረገው የዘመን ቅመራ ነው ፡፡

2ኛ. ዓለም በስምንተኛው ሺህ ዓመት ታልፋለች፤ ክርስቶስ ደግሞ ለፍርድ ይመጣል የሚል መንፈሳዊ ትምህርት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ከጥፋት ለመዳን፣ መንፈሳዊ ሕይወትን ለማስተካከል ሲባል ከጥፋት በፊት ዘመኑን ለማወቅ የተደረገው የዘመን አቆጣጠር ቀመር በ2ኛ ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡ በዚህም መሠረት እናውቃለን የሚሉ በተለያየ ዓለም የሚገኙ አንዳንድ ሰዎች ዓለም በዚህ ጊዜ ታልፋለች በሚል የተሳሳተ ቀመር ሕዝብን ማስደንገጣቸው የማይታበል ሐቅ ነው፡፡

3ኛ. ዓለማዊውን ምክንያት ስንቃኝ ደግሞ የሚከተለው በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ በዓለማችን ብዙ ነገሮች ተመላላሽ በመኾናቸውና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተመልሰው ከመምጣታቸውም ባሻገር ውጤታቸው በማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጣሪ መኾኑ የታወቀ ነው፡፡

ለምሳሌ ዕለታት በየሰባት ቀኑ፣ ወሮች በየ30 ቀኑ፣ ዓመታት በየ365 1/4 ቀኑ፣ ዐውደ ፀሐይ በየ28 ዓመቱ፣ ዐውደ አበቅቴ በየ19 (ንኡስ ቀመር) ዓመቱ፣ ዐውደ ማሕተም በየ76 (ማእከላይ ቀመር) ዓመቱ፣ ዓውደ ቀመር በየ532 (ዐቢይ ቀመር) ዓመቱ እየዞሩ ይመጣሉ፡፡ በመሬት እንቅስቃሴም ወቅቶች ይፈራረቃሉ፡፡ እያንዳንዱ ወቅት ደግሞ የራሱ የሆነ የአየር ጠባይ አለው፡፡ ብርዱ፣ ሙቀቱ፣ በረዶው፣ ዶፉ፣ ጎርፉ፣ ድርቁ ወዘተ. የመሳሰለው ሁሉ የራሱ የሆነ ዝግጅት ስለሚያስፈልገው የዘመን አቆጣጠር መፈጠር የሰውን ልጅ ከተፈጥሮ ቁጥጥር ውጭ እንዲኾን አስችሎታል፡፡ ምክንያቱም ድርጊቶች ወቅቱን ጠብቀው ቢከሠቱም የሚመላለሱበትን ዐውድ ተረድቶ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ችሏል፡፡ ወደ አቆጣጠሩ ስመለስ ብዙ የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት እንደሚያረጋግጡት በአውሮፓና በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መካከል የአቆጣጠር ዘዴው እንጂ በዘመኑ ልዩነት የለም የሚል ዋና ሐሳብ አለ፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ልዩነቱ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በፀሐይና በጨረቃ ሲኾን የአውሮፓ የዘመን አቆጣጠር ደግሞ በጨረቃ ብቻ ሥለሆነ ነው፡፡ በሁለቱም ዘዴ የዘመን አቆጣጠሩ ሲቀመር ተመሳሳይ ውጤት እንደሚያመጣ በምሳሌ ማሳየት የተሻለ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

1. በፀሐይና በጨረቃ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ቅመራ

5500 በሃይማኖታዊ እሳቤ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩት ዓመታት ናቸው ፡፡ ይህም የተገኘው

5.5 x1000 = 5500 ዘመን ነው፡፡ ይህም 5 ቀን ተኩል ⟹ ለአዳም የተሰጠው ተስፋ ነው፡፡ ይህ ዘመን በሌላ አባባል ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኵነኔ፣ ዘመነ ብሉይ፣ ዓመተ ዓለም እየተባለ ይጠራል፡፡ ምሕረት ወይም ድኅነት ያልተደረገበት ዘመን ስለነበረ ነው፡፡

1000 ዓመት ⟹ በእግዚአብሔር ዘንድ 1 ቀን ነው ተ ብ ሎ ይታመናል፡፡

2008 ዓመት ⟹ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ያለው ዘመን ሲኾን ይህም ዓመተ ምሕረት፣ ዓመተ እግዚእ፣ ዓመተ ሥጋዌ፣ ዘመነ ሐዲስ ይባላል፡፡

ከክርስቶስ ልደት በፊትና በኋላ ያለው ዘመን ሲደመር (5500+2008 = 7508) አንድነት ዓመተ ዓለም ተብሎም ይጠራል፡፡ በዚህ መሠረት ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ 7508 ነው ተብሎ በሃይማኖት ይታመናል፡፡ ይህ ግንዛቤ የመሬትን እድሜ በሚሊየን ከሚቆጥረው ከዘመኑ ሳይንስ ጋር ተቀራራቢ ኾኖ አይታይም፡፡ ነገር ግን ከላይ ባየነው አቆጣጠር አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት ከተቆጠረ ብዙም አይራራቅም ለማለት ያስደፍራል፡፡ ዓላማችን ይህ ስለአልኾነ ይህን በዚህ እንተወው፡፡

7508 በ19 ሲቀመር ⟹ 7508 ÷ 19 = 395.157

⟹ 395 x 19 = 7505 ንኡስ ቀመር ይሆናል፡፡ ቀሪው አይያዝም፡፡

7508 - 7505 (ከዓመተ ዓለሙ የተገኘው ንኡስ ቀመር ሲቀነስ) = 3 ይሆናል፡፡

3-1 = 2 ⟹ የ2008 ዓ.ም ወንበር 2 ነው ማለት ነው፡፡

አንድ የተቀነሰበት ምክንያት 2008 ተጀመረ እንጂ ስለአላለቀ ነው፡፡ ዐዋጁም አንዱን ለዘመን አስወግድ (ቀንስ) ይላል፡፡ ስለዚህ የ2008 ወንበር 2 ሆኖ ስለተገኘ ጥንተ አብቅቴውንና ጥንተ መጥቅውን በ2 አብዝተን እናገኛለን፡፡

የቀመር ስሌት በምሳሌ ሲታይ

2 x 11 = 22 ⟹ የ2008 አበቅቴ ነው ማለት ነው፡፡

11 7508 = 5500+2008 ዓመተ ዓለም ⟹ በፀሐይ ዓውደ ዓመትና በጨረቃ ዓውደ ዓመት መካከል ያለ ልዩነት ነው፡፡

የፀሐይ ዐውደ ዓመት ከጨረቃ ዓውደ ዓመት ሲቀነስ (365 - 354) = 11

ስለዚህ 11 አበቅቴ ወይም በፀሐይና በጨረቃ መካከል ያለ

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# ቀና ቀናውን

በመኳንንት ከተማ

የተከበራችሁ የናይል አዘጋጆች እና አንባቢዎች ሠላም ከረማችሁ? “እንቁጣጣሽ!” መቼም አዲስ ዓመት ሲመጣ አበባው ሲፈካ፣ ሸርጉዱ ሲበዛ አቤት ሲያስደስት አዲሱን ዓመት ምክንያት በማድረግ ሁሉም ሰው በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ እቅድ ሲነሳና ተስፋው በሃሴት ሲሞ መመልከት ምንኛ ያስደስታል፡፡

አሮጌውን ዓመት አሽቀንጥሮ አዲሱ ዓመት ሲተካ የሃገሬ ሰው “እንቁጣጣሽ!” እንኳን አደረሳችሁ፣ እንኳን አብሮ አደረሰን እየተባባሉ መልካም ሰላምታቸውን ሲለዋወጡ ማየት እና ሰላምታውን መጋራት ልዩ ደስታን ይፈጥራል፤ ምክንያቱም ይህ ታላቅ የመልካም ግንኙነት መገለጫ በመሆኑ ነው የሚል እምነት አለኝ ተደራሲያን መቼም በአዲሱ ዓመት መግቢያ ላይ እንደ መገናኘታችን መጠን የመንደርደሪያ ሃሳቤን ስለአዲስ ዓመት ሽታ እና ሸርጉድ ቅንጭብጭብ አድርጌ ማቅረቤ የሚከፋ አይመስለኝም፡፡ ለማንኛውም ግን አሁን ለዛሬ ማቅረብ የፈለግኩትን ሃሳብ ጭብጥ ልቀጥል ተከታተሉኝ በርዕሴ ላይ ቀና ቀናውን … አዎ “ቼር ተመኝ ቼር እንድታገኝ” እንዳሉት ቀና ቀናውን መስራት፣ ቀና ቀናውን መመኘትና ቀና ቀናውን ማሰብ ምንኛ ደግ ነገር ነው ጉበዝ! ታዲያ! ውድ አንባቢያን የሕይወት ስንክሳራችን ቀና ቀናውን ይገጥማት ዘንድ ቅን ሆኖ ቀናውን መተግበር አይበጅም ትላላችሁ? ግድ የለም ጀግና ቀና ቀናውን እንተግበር፤ ለዛሬ የማቀርብላችሁ ቀና ቀናውን መስራት የሚሰጠውን የመንፈስ እርካታ፣ የገፅታ ግንባታ እና የተገልጋይ እፎይታ ገጠመኝን ዋቢ አድርጌ ነው፡፡ ምን መሰላችሁ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ተገልጋይ እያስተናገደ ይገኛል፤ ይሁን እንጅ በየማዕከላቱ ወደ ዩኒቨርሲቲው የሚመጡ በርካታ ባለጉዳዮች የሚፈልጉትን መረጃ በአጭር ጊዜ ለማግኘት የግቢውን ማህበረሰብ ሲጠይቁ ደንበኞች በማን እና በየትኛው ቢሮ እንደሚስተናገዱ በትክክል አመላክቶ ከማስተናገድ ይልቅ በዛ ሂድ፣ በዛ ነው መሰል፣ ከዛኛው ግቢ ሂድ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት የማያረኩ እና ግድ የለሽ መሰል መልሶችን የሚሰጡ አንዳንድ ግለሰቦች እንዳሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች አጋጥሞኛል፤ “እውነት እውነት እላችኋለሁ” እንደሚባለው በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለተወሰኑ ደንበኞች ከሚፈልጉት አካል ድረስ በመውሰድ ግልጋሎቱን እንዲያገኙ እርዳታ በማድረጌ ያገኘሁት ምርቃት ሳይበሉ ያጠግባል፤ ይሁን እንጅ አንዳንዶቹን ደግሞ የጐሪጥ አይቼ ሲቸገሩ ባለመረዳቴ የእራስ ወቀሳ ይከሽክሸኛል፡፡ ምክንያቱም ባለጉዳዮች አገልግሎት ፈልገው ሲመጡ ወደዚህ መሩን፣ ከዚህ አካባቢ ነው ብለውናል ወ.ዘ.ተ እያሉ የፈለጉትን ሳያገኙ ጊዜ እየባከነባቸው ትክክለኛው ሰው እና ቢሮ ጠፍቷቸው ፊታቸውን ኮስኩሰው ሲጨናነቁ በመመልከቴ እና እኔም እስኪ ወደዛ ሂዳችሁ ጠይቁ የሚል ኮሳሳ መልስ በመስጠቴ ነው፡፡ ለማንኛውም ግን መረጃ ፈልጐ የመጣ ደንበኛ ትክክለኛውን መረጃ በተገቢው ሰዓት እንዲያገኝ ቀና ቀናውን በመምራት ለደንበኞችን እፎይታ፣ ለእኛም የመንፈስ እርካታ፣ የዩኒቨርሲቲያችንም መልካም ገፅታ ግንባታ ለማጉላት የምናውቀውን ሁሉ በቀናነት በማሳየት እና በመተባበር እንስራ ዘንድ የማንቂያ ደወሌን እንዲህ አስቀምጫለሁ፡፡

ውድ አንባቢያን ይህንን የመረጃ መረብ አሰጣጥ በጥልቀት ሳልገባ እንዲሁ ቅንጭብ አድርጌ በማለፍ ከዚህ ሃሳብ ጋር ተያያዥ በሆነ ጉዳይ ብጨምር ምን መሠላችሁ? አዲስ ዓመትን ተከትሎ የሚመጣ የተለመደ ክስተት ነገር ግን የጋራ እርብርብ የሚጠይቅ ነው፡፡

የአዲስ ተማሪዎች የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ይገርመኛል! ከቤተሰቦቻቸው፣ ከሀገር ከቀየው ወጥተው ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲቀላቀሉ አንዳንዶቹ ባይተዋርነት ሲሰማቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ወደ እስር ቤት የመጡ ያህል ይሰማቸውና ከጅምሩ መስመር ይስታሉ፡፡ መቼም ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲመጡ ከቤተሰቦቻቸው ታላቅ አደራ ተሸክመው ሰፊ ዓላማ አንግበው እና ታላቅ ተስፋ ሰንቀው ነገን በተሻለ ሕይወት ለመምራት አስበው እንደሚመጡ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በሲኒየር ተማሪዎች በቀላሉ መታለል፣ ወደ ከተማ ሽርሽር በማብዛት ለወጭ ከመዳረግ አልፎ ሲልም ወደ ተለያዩ ሱሶች በመግባት ከጨዋታ ውጭ የሚሆኑ ቀላል ቁጥር ያላቸው አይደሉም፡፡ በመሆኑም እነዚህን አዳዲስ ተማሪዎች ገና ሲገቡ ጀምሮ በአግባቡ በመቀበል እና ትክክለኛ መረጃ በመስጠት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በማዘጋጀትና በማስተማር ከአላስፈላጊ ወጭ እና የዓላማ ክስረት እንታደጋቸው ዘንድ ላሳስብ እወዳለሁ፡፡

ውድ ሲኒየር ተማሪዎቻችን በተለይም ወንዶቻችን አዲስ ተማሪዎች ሲገቡ ስልክ እየተቀበሉ ማሳደድ /መጀንጀን/፣ መንገድ ላይ መፎገር፣ ማሸማቀቅ እና ማስፈራራት ይቅርባችሁ አዲስ ገቢ ተማሪዎችን ትክክለኛ መረጃ በመስጠት፣ በማረጋጋት እና በመደገፍ እንድናግዛቸው ጥቆማዬን ሰጥቻለሁ፡፡ ሥለዚህ የተወደዳችሁ አንባቢያን እና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለሁሉም ነገር ቀና ቀናውን በማሳየት እና በመምራት የተስተካከለ የሕይወት መስተጋብር በመፍጠር ግንኙነታችን በመልካም ስም እንገንባ እያልኩ፤ ጽሑፌን አንብባችሁ ወደ ተግባር ትተረጉሙት ዘንድ እያሳሰብኩ የዛሬውን በዚህ አበቃሁ ሠላም!

# Code Switching as ...

continued from page 5

In this connection, Stephen Kalong (2008) claims that in a multi-lingual classroom, students who do not have the same mother tongue might feel neglected by the application of code switching in their classroom. She further suggests that code switching can be used effectively in a classroom where all students have the same main language. Moreover, after examining the various positions on the role of language in education, Bernardo (2005) concludes that assumptions to use code-switching may not be tenable particularly in a multilingual global context. Based on these assertions; therefore, I argue that code-switching may not be feasible, for it has the potential to discount the legitimacy and realities of Ethiopian multilingual context.

Consequently, we can realize that code choice in this situation might be a very sensitive issue that we need to take into consideration seriously. On the other hand, there is no doubt that we are not equally and professionally competent in translation. Unlike other teaching approaches, translation requires one to possess sophisticated skills and experience without which more problems and confusions could be created for our students. On balance, I am not claiming that translation has no place in teaching in multilingual settings. In fact, I don't totally disregard the greatest virtues of switching codes. However, I contend that at the expense of code-switching, other teaching methods like student-teacher conferencing, experience sharing can be used to foster teaching. Now let me pose this question: As an Ethiopian university instructor, have you ever empathized strongly how painful it may be when you were unable to communicate with your teacher, for you did not know the language he or she switches into? To me, this question remains in my mind echoing again and again as it is inherent within the essence of the teaching profession.

In a nutshell, code-switching has potentially both positive and negative consequences. Taking every possible outcome into account, I would like to propose that we should not consider code-switching as a compromise option for the complexity of the language competencies. Instead, to overcome the possible English language shortcomings in the classroom, better investment in the proper utilization of classroom English is needed to enhance the teaching pedagogy. Above all, I argue that translation needs to be used as the last opportunity after the teacher tries every available means that helps students learn best, for its disadvantages outweigh its advantages.

## የማህበረሰቡን የጤና ችግር …

ከገጽ 4 የዞረ

የጤና ችግር ለመፍታት ከፍተኛ አቅም እንዳላቸው ተገልጿል፡፡

እነዚህ የማህበረሰቡ የጤና ችግሮችን በመንግስት ተለይተው የተቀመጡና የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ በመሆን ኮሌጁ በዚህ ዙሪያ የሰሩ ተመራማሪዎችን በመጋበዝ የምርምር ጉባኤው እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኮሌጁ በአራት የመጀመሪያ ዲግሪ እና በአራት ድህረ ምረቃ መርኃ ግብሮች ያሉት ሲሆን ኮሌጅ በ2007 የበጀት ዓመት በ140 መምህራን ለ1682 ተማሪዎች በመቀበል ስልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡ በ2008 ዓ.ም ተማሪዎችን በመቀበል አዲስ እያስገነባ ባለው የሰባትአሚት ግቢ ትምህርት ለመስጠት ቅድመ ዝግጅቱን ማሟላቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ፌዴሬሽኑን ለማጠናከር

… ከገጽ 4 የዞረ

ተናግረዋል፡፡ አምባሳደሯ አያይዘውም ለወደፊት በሴቶች ዙሪያ ተቋማዊ የሆነ ለትውልድ የሚተላለፍ አኩሪ ሥራ ለመሥራት ዲያስፖራዎች የረጅም ጊዜ ልምዳቸውንና አቅማቸውን በመጠቀም ሴቶችን ማብቃት እንዲችሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ በውይይቱ ላይ የክልሉ ታዋቂ ሴቶች፣ ሴት ዲያስፖራዎችና አምባሳደሮች የተሳተፉ ሲሆን ጥናታዊ ፅሁፍ ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡ ተሳታፊዎችም ሴቶች መምራትና ሀገር ማልማት እንዲሁም ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ ከውይይቱ የጋራ ግንዛቤ ማግኘት መቻላቸውን ገልፀዋል፡፡ ተሳታፊ ዲያስፖራዎች ለወደፊት ለሀገራቸው የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ለመፈጸም ቃል ገብተዋል፡፡

# ተጋቦት

በደስታ ተከስተ
ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት
ደስታተከስተ4@gmail.com

አቶ አንድሮ አገቡ፤ መቼም ይህን ብዬ ስጀምር እናንተ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን ግር መሰኘታችሁ አይቀርም፡፡ በባህሪዬ ቂምና ሰላምታ ስለምዘነጋ ወጌን በሰላምታ አልጀመርኩም፡፡ ያምሆነ ይህ ወዲህም ሆነ ወዲያ ... ዋናው ጉዳይ ፅሑፍ መፃፍ የመጀመሪያዬ ነውና ይኸው ከመፃፌም ባሻገር እናንተም ማንበብ ጀምራችኋል፡፡

አቶ አንድሮ ምን አገቡ? እንዴት አገቡ? ማግባታቸው ምን አዲስ ነገር አለው? የሚሉትን ጥያቄዎች ከማብራራቴ በፊት አቶ አንድሮ ማን ናቸው? የሚለውን ሃሳብ ሳልጠየቅም ቢሆን ማውጋት እወዳለሁ፡፡ እኔ ፀሐፊው ካሣ ደፋሩ አቶ አንድሮን የማውቃቸው ነፍስ ካወኩ ወዲህ ነው ከእርሳቸው ጋር ትውውቃችን የጠበቀ ቢሆንም በሃሳብና በምግባር የሁለት ዓለም ሰዎች በመሆናችን ተቃርኗችንም የትየለሌ ነው፡፡

አቶ አንድሮ የተወለዱት አዬው ከአልጋ ሲወጡ ነው ይባላል፤ አዬው አልጋ የወጡት መቼ ነበር? ለሚለው ፀሐፊው የሚያውቀው መረጃ ባይኖርም ግምቱን ግን ማስቀመጥ ይችላል፡፡ ምናልባት አዬው ለመጀመሪያ ቀን ከመደብ መኝታ ላይ ወደ አልጋ መኝታ የተሸጋገሩበት ዕለት ሊሆንም ይችላል... ይኸ ፀሐፊ... ይቃዣል እንዴ? ለመሆኑ አቶ አንድሮ የተወለዱት በየትኛው አዬ ዘመነ መንግስት ነው? በኢትዮጵያ በርካታ አዬዎች እንደነበሩ እናውቃለን የሚል አንባቢ መከሰቱ ስለማይቀር ለዚህም ጥያቄ እኔ ካሣ ደፋሩ ከመገመት ውጭ እርግጡን ለመናገር አልደፍርም፡፡ እንደሚታወቀው እኔም በታሪክ ከማውቃቸው አዬዎች መካከል ... አዬ ልብነ ድንግል፣ አዬ ኃ/ስላሴ ... እንደነበሩ ነው የታሪክ ተመራማሪው ባልንጀራዬ ሲተርክልኝ እንደሰማሁት፡፡ እናም አቶ አንድሮ ከነዚህ አዬዎች የንግስና ዘመን በአንዱ እንደተወለዱ እገምታለሁ፡፡ ወጣም ወረደ የአቶ አንድሮ እድሜ የዛፍ እድሜ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል (አንባቢዎቼ መቼም የዛፍ እድሜ ምን ያህል እንደሆነ ታውቃላችሁ ብዬ ነው)፡፡ የት አካባቢ ተወለዱ? የየትኛው ብሔረሰብ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው የሚሉት ጥያቄዎች መልስ በአጭሩ አቶ አንድሮ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ሀበሻ ናቸው፡፡

ለመሆኑ እኚህ የእድሜ ባለጠጋ አንጋፋ ኢትዮጵያዊ ሀበሻ ይህን ያህል ዘመን ሲኖሩ ለሀገር ለወገናቸው ምን ሥራ ሰሩ? በምን ይታወቃሉ? ለሚለው ጉዳይ ፀሐፊው ካሳ ደፋሩ ያለ ጭፍን ተቃውሞ፣ ያለ ጭፍን ድጋፍና ያለስሜታዊ ወገንተኝነት በነፃ አስተያየት እውነት የሆነውን አወጋችኋለሁ፡፡

የአቶ አንድሮ የትምህርት ዝግጅት በዘመናቸው ሲታወስ አቦጊዳን ጨርሰው መልክተ ዮሐንስን እንዳጋመሱ ሀገሪቱ የውጭ ወራሪ ጠላት ስለገጠማት ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ጦር ሜዳ ዘመቱ፡፡ የመማራቸው ነገር እዚያው ላይ አክትሟል፡፡ በእርግጥ አቶ አንድሮ በጦርነት ወቅት በጀግንነትና በጨዋነታቸው ሀገሪቷን ከወራሪ ጠላት ጠብቀው በማቆየታቸው አንቱ የተባሉ ጀግና ወጥቷቸዋል፡፡ በእድሜ ዘመናቸው ከሚታወቁበት አንዱ ታሪካቸውም ይህ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ አቶ አንድሮ "ነበር ድሮ" የተሰኘ መጽሐፍ ጽፈው አሳትመዋል፡፡ ችግሩ ግን ... የመጽሐፉ ደራሲ እሳቸው ሲሆኑ አንባቢውም እሳቸው መሆናቸው ነው፡፡ "የእርስዎን መጽሐፍ ለምን ሰው አያነበውም?" ተብለው ሲጠየቁ "ኤዲያ! ምን አንባቢ አለና ነው? አንባቢና ንባብ ድሮ ቀረ! አይገባቸውማ! አንብቦ የሚገባው ሰው ድሮ ቀረ!" በማለት የዛሬውን ዘመን ሁለንተና እያጣጣሉ የወደፊቱን ተስፋ በማጨለም የድሮውን ብቻ እያደናነቁ ይኖራሉ፡፡

ውድ አንባቢዎቼ! እንግዲህ ከእኔም ከፀሐፊው ጋር የልዩነታችን ተራራ ይህ የአቶ አንድሮ "ድሮ ቀረ" የሚባለው አመለካከታቸው ነው፡፡ እኔ ለራሴ ተስፈኛ ነኝ፡፡ ለትውልዱና ለእናት ሀገሬ ኢትዮጵያ የሚበጅ ራዕይ አለኝ፡፡ ከራዕዮቼም መካከል ገሚሶቹ እየተፈፀሙ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ተስፋዬ ይበልጥ እየጨመረ ራዕዬም እየሰፋ ነው፡፡ በእርግጥ ከድሮ ታሪኮች ለዛሬ መነሻዬ ለነገ ተስፋዬ እውን መሆን ለራዕዮቼ ፍፃሜ የሚረዱኝን ጠቃሚ ሀሳቦች ብቀስምም "በድሮ በሬ ያረሰ የለምና" እንደ አቶ አንድሮ "በድሮ" አላመልክም "ሽማግሌ በትዝታ ወጣት በተስፋ ይኖራሉ" የሚሉትን አባባል እውነታነት ያረጋገጥኩበት በእኔ በወጣቱና በሽማግሌው በአንድሮ ሁኔታ ነው፡፡

እርሳቸው ውሎአቸው ጠጅ ቤት ወሬአቸው "ድሮ ቀረ" ሲሆን ስለ ድሮ ነገር ጀምረው እዚያው ድሮ ላይ ያቆማሉ፤ ዛሬም ሆነ ነገ አይታያቸውም፡፡ እየጠጡት ያለውን ጠጅ እንኳን "ኧረ ... ኤዲ...ያ! እቴ ... ጠጅ ድሮ ቀረ!" በማለት ያጥላሉታል፡፡ ስለ አሁኑ ትውልድ ሁኔታ ያላቸውን ምልከታ አስተያየት ሲጠየቁም "አ...ይ...ይ ስለየቱ ትውልድ? ምን ትውልድ አለ ደግሞ! ትውልድ ድሮ ቀረ! ድሮ በእኛ ጊዜ" ይላሉ፡፡ ለአቶ አንድሮ ሀገሪቷን ለማልማት ደፋ ቀና የሚለው ዜጋ ትውልድ አይደለም፤ አስፋልት መንገድ የሚሰራው መሀንዲስ ትውልድ አይደለም፤ ይገርማችኋል እኮ! እናንተዬ አቶ አንድሮ በተንጣለለው አስፋልት መንገድ ላይ እየተራመዱም "ኧረ ... ኤዲያ...አስፋልት መንገድ ድሮ ቀረ ድሮ ቀረ ... በአዬው ጊዜ"፤ በዘመናዊ ሞባይል ስልክ እየተነጋገሩ "ኧረ ወዲያልኝ ሞባይል ድሮ ቀረ ... ድሮ በእኛ ጊዜ"፤ በወጣቱ ዶክተር እየታከሙ "ዛሬ ጊዜ ምን ዶክተር አለና ነው! ... ዶክተር ማለት ድሮ ቀረ"፤ የአዲሱን ትውልድ ባለስልጣናትን ሲሰሙም "ኧረ ኤዲያልኝ እቴ! አይ ንግግር! ንግግርና ባለስልጣናት ድሮ ቀሩ ... ድሮ በእኛ ጊዜ ድሮ በእነአዬዎች ዘመነ መንግስት፤ ዛሬ በዚህ ዘመን ምን ተናጋሪ ሹም አለና ነው? የለምኮ!" ይላሉ፡፡

**"አይ...ይ ወንድሜ ሆይ አይጣልብህ ... ትዳርና ሽማግሌ ድሮ ቀረ" አለችና ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ጓዳዋ ዘለቀች በተቀመጥኩበት ... ሁኔታው ከነከነኝ**

አቶ አንድሮ አሁን በዚህ ሰዓት ይህን የጋዜጣ ፅሑፍ እያነበቡ ቢሆን "አይ...ይ ጋዜጣና ፅሑፍ እቴ! ኤዲያ ! ጋዜጣም ፀሐፊም ድሮ ቀረ" ማለታቸው አይቀርም፡፡

ውድ አንባቢዎቼ! እስቲ እንደው አቶ አንድሮ ሲናገሩ ካስገረሙኝ ነገሮች ጥቂቱን ላካፍላችሁ፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን ታላቁን የህዳሴ ግድብ በዓባይ ወንዝ ላይ ለመገንባት የመሰረት ድንጋይ በተጣለበት ቀን እኔና ባልደረቦቼ እንዲሁም ትውልድ ሁሉ ደስታውን በሚገልፅበት ወቅት ጋዜጠኞች የህብረተሰቡን አስተያየት በማሰባሰብ ላይ እያሉ እንደ አጋጣሚ ሽማግሌው አንድሮ በካሜራ እይታ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይህን ጊዜ ጋዜጠኛው "አባት ስለሚገነባው የህዳሴው ግድብ ምን አስተያየት አለዎት?" ሲላቸው "አይ ልጄ ጋዜጠኛም ሆነ የሕዳሴ ግድብ አድሮ ቀረ!" በማለታቸው እሳቸው የሰጡት ሃሳብ ከነምስላቸው በቴሌቪዥን ሳይተላለፍ ቀረ፡፡

እንዲሁ አንድ ዓመት ላይ ደግሞ የዓለም ኤድስ ቀን ሲከበር ከአንድ ጠያቂ ጋዜጠኛ ጋር ተገናኝተው "ለመሆኑ እርስዎ እንደ አባት ለወጣቱ ትውልድ እራሱን ከኤች.አይ.ቪ ቫይረስ እንዲከላከል ምን ይመክሩታል?" በማለት ሲጠይቃቸው "ኧረ ተወኝ ጋዜጠኛ! ዛሬ ጊዜ ደግሞ ምን ኤድስ ቫይረስ አለና ነው? ኤድስ ድሮ ቀረ!" በማለታቸው ከዛን ዕለት ጀምሮ እኔ ፀሐፊውን የአቶ አንድሮ እርጅናቸውና የጤንነታቸው ሁኔታ በእጅጉ ሲያሳስበኝ ከርሟል፡፡

እንግዲህ አቶ አንድሮ ማለት ከብዙ በጥቂቱ እኝህን ይመስላሉ፡፡ አሁን በቅርቡ ደግሞ ሰይጣን ይሁን መላዕክ ምን እንዳሳያቸው ሳይታወቅ ካላገባሁ ብለው ተነሱ፡፡ መቼም አንድሮ የኳስ ጨዋታ ጐል ወይም የተሰጣ ልብስ ላስገባ ብለው እንዳልሆነ ለአንባቢው ግልፅ ይመስለኛል፡፡ ያው እንግዲህ በዘመድ አዝማድና በንስሃ አባት ተመክረውም ተገስፀውም አሻፈረኝ በማለታቸው መፅሐፉም ሆነ ህጉ ባይፈቅድም ከሞራላቸው አኳያ ታይቶ ቢያገቡ ባልከፋም ነበር፡፡ እሳቸው አገባታለሁ ያሏት ሴት ኢ.ህ.ዲ.ግ የአዲስ አበባን ከተማ በተቆጣጠረ በዓመቱ የተወለደች ወጣት መሆኗ ነው፡፡ "ያላቻ ጋብቻ እንዴት ሆኖ?" ቢባሉም ሞቼ እገኛለሁ ስላሉ ይሁን ተብሎ አገቡ፡፡ ለመሆኑ ወጣቷስ እንዴት "እሺ" አለቻቸው ብትሉኝ እንዴት ፈቃደኛ እንደሆነች እኔ ካሣ ደፋሩ ሰዎች በስሜት አንዳንድ ጉዳዮችን ሲናገሩ ከመስማት ውጭ በቂ የሆነ መረጃ ስለሌለ ምንም ላለማለት ተቆጥቢያለሁ፡፡

በበኩሌ ስለአንድሮ ማግባት ሁለት አይነት ሃሳብ አጭሮብኝ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ሃሳቤ ልጅቷ ወጣት በመሆኗ ምን አልባት ሽማግሌው አንድሮ "ድሮ ቀረ" የሚለውን አመለካከት ለውጠው አዲስ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ሊያራምዱ ይሆናል በማለት ነገሩን በአዎንታ መልኩ ስመለከተው ሁለተኛው ሃሳቤ ስጋትን ያዘለ ሲሆን ለመሆኑ አቶ አንድሮ በዚህ እድሜአቸው የአልጋ ላይ የፍቅር ጨዋታ ይሆንላቸዋል ወይ? የሚል ነበር፡፡ እነዚህን ሃሳቦች በልቦናዬ ሳብሰለስል ሰንብቼ ከዕለታት በአንድ እሁድ ቀን ከቅዳሴ መልስ እግረ መንገዴን ወደ አቶ አንድሮ ቤት ለጥያቄ ሄድኩ፡፡

የከበረና የጠበቀ ሰላምታዬን ካቀረብኩ በኋላ እንደ ወዳጅነቴ "አቶ አንድሮ እንዴት ነው አዲሱ ትዳር ተመቸዎት ወይ?" በማለት ስጠይቃቸው እረኝዥም ጢማቸውን እያፍተለተሉ "ኧረ ኤዲያልኝ! ተወኝ እስቲ ወዳጄ! ሴትም ትዳርም ድ... ድሮ ቀረ!" አሉኝና ከዘራቸውን አንስተው ቤቱን ለቀው ወጡ፡፡ በሰዎች መካከል ባለ አለመግባባት ስለትዳር ሁኔታ ከአንድ ወገን ብቻ ያለውን ሃሳብ ሰምቶ እውነታውን ማረጋገጥ አይቻልምና ወጣቷን ወ/ሮ "እንዴት ነው ትዳር ሽማግሌው ባለቤትሽ እየተመቼሽ ነው?" ስል ጠየኳት፡፡ እርሷም ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ከተከዘች በኋላ "አይ...ይ ወንድሜ ሆይ አይጣልብህ፡፡ ትዳርና ሽማግሌ ድሮ ቀረ!" አለችና ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ጓዳዋ ዘለቀች፡፡ በተቀመጥኩበት ሁኔታው አስደመመኝ፡፡ የአቶ አንድሮ አመለካከት በወጣቷ ሴት ውስጥ መጋባቱ ቢያንገበግበኝ አንድሮ አባቴ እግዜር ይይሎዎት! በማይመጣ "ድሮ" ትውልዴን በከሉት አልኩኝ ለራሴው፡፡ በሉ እንግዲህ ውድ አንባቢዎች ለዛሬው ወጌን በዚህ ላብቃ፡፡

"ድሮ" እያለ የዛሬን ምግባራችሁን ከሚያኮስስ የነገ ራዕያችሁን ከሚያጨልም ሰው ተጠበቁ!

# የሽማግሌው ኑረት

አትክልት ዳኛው የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ግቢ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ባለሙያ

‹‹ሰው ብቸኛ የሚባለው ሰው በሌለበት ቦታ መኖሩ ብቻ አይደለም›› እንዲያውም ብቸኛ የሚለው ቃል ከሌሎች ጋር ውህደት ለመፍጠር መቸገርን ይህም ማለት ከሰዎች ጋር እየኖሩ ሀሳብን ተጋርቶ ለማጋራት እና ስሜትን ለመናበብ ሳይቻል ያኔ ነው ብቸኛ የሚለው ቃል ትርጉሙ የሚገባን›› በማለት እያሰላሰለ ሁሌም በተመስጦ ወደ ሚመላስበት ቦታ አመራ፡፡ ይህን ቦታ ለራሳቸው ‹‹አምላክን መገናኛ›› ብለው ሰይመውታል፡፡ መቼም ስም ለመሰየም ጋሼ ዮሴፍ ባህሉ እንደሚፈቅደው ዳቦ ማስቆረስ፣ ሻማ ማብራት፣ ህጉ እንደሚያስገድደው ማህበራዊ ፍርድ ቤት መሔድ አያስፈልጋቸውም፡፡ የራሳቸው የሆነ ፍርድ ቤት፣ ትምህርት ቤት፣ ቤተ አምልኮ፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ ወዘተ ብለን የምንጠራቸውን ሁሉ በአንድ ቦታ ፈጥረው አካልን አስገዞ እና አሳድሞ፣ ስሜታቸውን ከቦታዋ ጋር አላምደው፣ መንፈሳቸውን አዋህደው የመኖር ጥበብን አዳብረዋል፡፡ እዚያው አምለክን መገናኛ ከሚሏት ቦታቸው በእርግጥ ቦታው በሀይቁ ዳርቻና በጫካ የተከበበ ስለሆነ አምላክ ሁሉም ቦታ ይገኛል ብለን ካመን ሽማግሌው ዮሴፍ አምላክን ትተው ሌላ ሰብዓዊ ፍጡር ሳይጋራቸው ለብቻቸው እንደሚያገኙት አይጠራጠሩም፡፡

ሽማግሌው ዮሴፍ ወደ ተመስጦ ቦታቸው ሲሔድ ሁሌም በቀኝ እቅፍ ነጭና ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላት ድመት በትከሻቻው ማንም በውስጡ ምን እንዳለ የማይታወቅ በባህላዊ መንገድ ከቆዳ የተሠራ ቦርሳ ያነግታሉ፡፡ በእርግጥ ብዙ ሰዎች ሽማግሌውን ንክ ናቸው የሚል መደምደምያ ላይ ደርሰዋል፡፡ እንዲያውም ንክ የሚሉት ትንሽ ለሞራላቸው አሰብን የሚሉ ‹‹ጠንቃቆች›› ናቸው እንጂ ሌሎች ገና ገፀ ሠውነታቸውን በማየት በተፈጥሮ እብድነትና ነዳያነትን እንደእጣ ፋንታ ተዳብለው የተሰጡት መሆኑን አምናው የላይና የታች ከንፈራቸውን በመጭመቅ ‹‹እመጽ›› በማለት ሩህሩህ መሆናቸውን ለራሳቸው አውጀው ሌሎች እንዲያዝኑላቸው ጥቆማ ቢጤ ለምፀት በሚመስል ገልመጥ ገልመጥ ብለው አይተው ራሳቸውን ወዝውዘው ‹‹እንዲህ ከንቱ ሆነህ ቀረህ›› እይታ አይተው ይሸኙታል፡፡ ግን ሽማግሌው የዛ ሰው አይደሉም፡፡ ሁሉም ነገር የሚገባቸው ባለፈጣን አዕምሮ ባለቤት ናቸው፡፡ በል ሲላቸው ከንፈራቸውን ለሚመጡላቸውና ራሳቸውን የሚወዘውዙላቸውን ሰዎች አስመሳይነት፣ አዲስ ሃሳብና ድርጊት ፍራቻ፣ ራስን በገደብ ውስጥ ወስኖ አለምን አስፈሪ አድርጎ የማየት አባዜ፣ ራስን እየሸነገሉ መኖራቸው፣ እውነታን ለመጋፈጥ ዝግጁ ያለመሆናቸው ያሳየ ነው እና እነዚህን አሳዛኞች ህይወታቸውን ለመታደግ ምን ማድረግ አለብኝ በሚለው ሀሳብ ማብሰልሰል ይጀምራሉ፡፡ በዚው ቅፅበት ፈገግ ይላሉ፡፡ የሽማግሌው የፊት መስመሮች ቀስ በቀስ ሰፋ እያሉ፣ በፀጉር የተሸፈኑ ከናፍሮቻቸው ወደ ላይ መግለጥ ሲጀምሩ አካላዊ እርጅና ያወየባቸው ጥርሶች በገሃድ ሲገለጡ ሰውየው በወጣትነታቸው ምን ያህል መልከ መልካም እንደነበሩ ለመገመት አያዳግትም፡፡ ወደ ፈገግታቸው እንመለስና የፈግታቸው ምንጭ ለሽማግሌው የሚያዝኑት ሰዎች ሽማግሌውን ለመርዳት እና የተሸለ ኑሮ ለማኖር ገንዘብ ፈልገዋል በሚለው የመፍትሔ ሃሳብ ቢሰማሙም የሚችሉትን ለማድረግ ፈቃደኞች አለመሆናቸውን፣ አስመሳይነታቸውን፣ የማያምኑባትን ኑሮ መኖራቸውን ሲያስተውል ሽማግሌው ለእነሱ ያዝንሉቸዋል፡፡ ‹‹አዝነው ሲያልፉ ለምን ራሳቸውን እንሚሸነግሉ አይገባኝም? በማለት ይነጫነጫሉ፡፡ ከውስጣቸው ከሆነ የሚናዝኑት ለምን አይኖሩትም? ለምን በእነሱ ቤት ደስተኛ ያደርገዋል ያሉትን ምንዳ እንኳን ለመስጠት ድፍረት ያንሳቸዋል? ሲሉ ከራሳቸው ጋር ይከራከራሉ፡፡ ቆይተውም እያንዳንዳችን በተለያዩ ተክለ ሰውነትና አስተሳሰብ የተፈጠርነው እኮ እነሱ እነደሚኖሩት በቡድን ለማሰብ፣ ተዳብሎ ለመኖርና በገደብ ለመኖር አልነበርም፡፡ ስለዚህ እያንዳንዳቸው የተለየ አፈጣጠር እንዳላቸውና የህይወት ግባቸው ሌላው ያሰበው ብቻ ሃሳብ ማሰብ፣ ሌላው ያደረገውን ብቻ አድርጎ ማለፍ ሳይሆን ወደ ምድር መምጣታችን በቂ ምክንያት እንዳለው አለመከወን ደግሞ የፈጠረንን ሥራ ከንቱ ማድረግ መሆን በምን ሁኔታ ባስረዳቸው ይገባቸዋል ብለው አንድ እርምጃ ቀድመው ማሰብ በመቻላቸው ፈገግ አሉ፡፡ እንዲህ አይነት ሃሳብ ሲመጣላቸው ልማድ አድርገውታል፡፡ መቼም ለመሳቅ ግድ አብሮ የሚያሳስቀን ደባል የግድ አያስፈልግም አሉ ሽማግሌው፡፡ ሽማግሌው ‹‹አምላክን መገናኛ›› ከሚሉት ቦታ ሲመላለሱ የማህበረሰቡን የኑሮ ሁኔታ፣ አጠቃላይ እንቅስቃሴና ጥቃቅን ለውጦችን ሳይቀር ያጤናሉ፡፡ በአንድ ምሽት ሰዎች ‹‹እንዲህ ሆነህ ቀረህ›› አይነት ሀዘኔታ ሲያዝኑላቸው መመልከት የለመዱት ቢሆንም የተለየ ትኩረት እንዲሰጡት ያስገደዳቸው አንድ ተማርኩ የሚል ጎልማሳ የተናገረው ንግግር ነበር፡፡ ጎልማሳው ‹‹አባ ለምን ወደ አማኑኤል ሄደው የአዕምሮ ህክምና አያደርጉም›› በማለት ስለ አማኑኤል የስነ-አዕምሮ ህክምና መረጃ ያለው በመሆኑ ኩራት እየተሰማው ተናገረ፡፡ ሽማግሌው ይህን ጥቆማ ማለፍ ተሳናቸው፡፡ ‹‹ለመሆኑ የኔ ልጅ አሁን የጠቆምከኝ ቦታ የት ሠፈር ነው?›› ጎልማሳውም ‹‹አይ ቦታው እንኳን ከሰው ጋር ካልሔዱ ለእርስዎ ይከብዳል ያው አዲስ አበባ ነው፡፡ እዛ ደግሞ ያውቃሉ አንደርስዎ ያለ የአዕምሮ በሽተኛ ይቀርና ጤነኛውም ሰው ካልለመደው ይከብዳል፡፡›› ‹‹ለመሆኑ የኔ ልጅ ስለ እኔ የአዕምሮ ህመምተኛነት ስትነግረኝ አንተ ጤነኛ መሆንህን እርግጠኛ ነህ?›› በማለት ጠየቁት፡፡ ጎልማሳውም ስለ ራሱ ጤንነት በመጠራጠሩ ግራ በመጋባት ትቷቸው ሄደ፡፡ ሽማግሌውም በበኩላቸው በዚህ እድሜ ያለ ሰው ራሱን ፍፁም አድርጎ ማሰብ ከጀመረ ለለውጥ እና አዲስ ሃሳብን ለመማር ዝግጁነት ያንሰዋል፡፡ ስለዚህ መሥራት ያለብኝ የህፃናትን ስብዕና መገንባት ማለትም ስለ ዓለም ያላቸውን ግንዛቤ ማዳበር፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደምወዳቸው በተግባሬ ማረጋገጥ እና ጓደኛቸው መሆኔን እንዲሰማቸው ማድረግ፣ አወንታዊ አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ ማገዝ ይሆናል፡፡ እድሜያቸው የገፉትን ለመለወጥ መሞከር ደረቅ እንጨትን ማረቅን ያህል ከባድ ነው አሉ ሽማግሌው ለራሳቸው፡፡ ሽማግሌው እንደ አብዛኛው ብቸኛ ሰዎች ስለ ሰው ያላቸው ስሜት በጥርጣሬ የተሞላ፣ ይጎዱኛል በሚል ስሜት የተቃኘ እና አግልለውኛል በሚል እሳቤ የፀዳ ነው፡፡ እንዲያውም ሰውን ሲወቅሱ እና ሲያማርሩ አይዳምጡም፡፡ እንዲያው ሽማግሌው ራሳቸውን ከዚህ ግርግር እንዳገለሉ በኩራት ይመሰክራሉ፡፡ ለዚህ አስረጅ አንዳንድ ምሽት ህፃናትን ሰብስበው የቆዳ ቦርሳቸውን እንደነገቱ ድመቷን በእግራቸው መካከል እንደያዙ ‹‹ጀግና ማለት ለሚያምንበት መስዕዋት የሚከፍል፤ የማያምንበትን የሚቃወም ነው፡፡ አዋቂ ማለት ራሱንና ተፈጥሮን የሚመረምር የራሴን ሃሳብ ብቻ ነው ትክክል በማለት የማይመፃደቅ፤ የሌሎችን ሃሳብ የሚያከብር፣ በቡድን ከማሰብ አባዜ ራሱን ያላቀቀ ነው›› ብለው ረጅም ንግግር ይጀምሩና የሚናገሩት ለህፃናት መሆኑ ትዝ ይላቸውን ግራ ቀኝ ፊት ኋላ አካባቢውን አማትረው ትንንሽና ጥቋቁር አይኖቻቸውን ሩቅ ወደ አድማስ አስወንጭፈው ረጅም ጺማቸውን እየጎነተሉ ሲስብ የሕፃናት ድምፅ አባነናቸው፡፡ አበባ ተረት አውራልን አለ አንዱ በጓደኞቹ ዘንድ ደፋር ተደርጎ የሚቆጠረው አሠፋ፡፡ ሁሌም እንዲህ ነው … ጓደኞቹ እንደ ፍላጎታቸው እንደሚላ አሰፍስፈው አይን አይኑን ያዩታል፡፡ እሱም በልምድ ይረዳቸውና የመጠየቅ ፍላጎቱ ካየለ ድርድር ሳያስፈልግ ይጠይቃል፡፡ ብዙዎቹ አንገታቸውን ከላይ ወደ ታች በመነቅነቅ ለእውነትነቱ ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ እይታቸውን አይቶ ችላ ሲላቸው ከግራ ቀኝ ይጎሳሰሙታል ወይም ደግሞ በአንድ ነገር ቅድሚያ እንደሚሠጠው ቃል ይገቡለታል፡፡ አሰፋም ይህ በጓደኞቹ ዘንድ ተፈላጊነቱን የሚያረጋግጥለትን እና የተሸለ ደፍር ያደረገውን የመጠየቅ ልማድ የእሱ የሥራ ድርሻ አድርጎ ማንኛውም ሃሳብ ወደ አዕምሮው ሲመላለስ ያለምንም መሸማቀቅ መጠየቅ ልማድ አድርጎታል፡፡ በድጋሜ ‹‹አበባ ተረት አውራልን?›› አለ አሰፋ ሌሎችም አብረው ተረት አውራልን እያሉ ወተወቱት፡፡ ሽማግሌው ‹‹ከአሁን በፊት ብዙ ቀን ተረት አወራችኋለሁ፡፡ ታድጋላችሁ ብዬ ብጠብቅም ጊዜው ረዘመብኝ፡፡ ማን ያውቃል ወይ የውስጤን ሳልነግራችሁ ሞት ሊቀድመኝ ይችላል፡፡›› ብለው ሲነገሩ ከህፃናቱ መካከል ሀፍረት የተቀላቀለበት ሳቅ ተሰማ፡፡ ሽማግሌው ወደ ልጆቹ ተመልክተው ማን እንደሳቀ አስተዋሉ፡፡ ሳቁ የተጋባባቸው በሚመስል ሁኔታ ፈገግ አሉ፡፡ ቀጥሎም ‹‹የኔ ልጅ ምን አሳቀሽ›› ብለው ወደፊት ሀመራዊ ፀጉራን መሻሸት ጀመሩ፡፡ ልጅቷ ግን ለመናገር ፈርታ ሳይሆን አፍራ እየተሽኮረመመች ‹‹እንዴ አበባ እርስዎ ትልቅ አይደሉ ሞትን ይፈራሉ?›› ስትል በሽማግሌው ፍርሃት ሁሉም ሳቁ፡፡

ꙮꙮꙮꙮꙮꙮ

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ …

ከገጽ 6 የዞረ

ሚሚያ የሚሆን ብር 3000.00 (ሦስት ሺ ብር) በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በኩል ልኬልሃለሁ፡፡ ካነሰህም ሁኔታውን ጻፍልኝ፡፡

የሚል ነበር ደብዳቤውን አንብቤ እንደጨረስኩ ብዙ ነገሮች ተዘበራረቁብኝ፡፡ እናቴ ምን ማለቷ ነው? እንዴት ይሆንላታል? እያልኩ በሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ስላለን ወደዚያው ለመሄድ ብቸኩልም እንደገና ደብዳቤውን እየደጋገምኩ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ ቀና ስል ከሄርሜላ ጓደኞች አንዷን ከፊት ለፊት ወደ እኔ ስትመጣ አገኘኋት፡፡ በልቤ ሰላም ልበላትና ሔርሜላን ልጠይቃት ወይስ ዝም ብዬ ልለፍ እያልኩ ከአዕምሮዬ ጋር ስሟገት እሷ ቀድማ በፈገግታ ታጅባ ሁለት እጆቿን ዘርግታ ሰላምታ ስታቀርብልኝ እኔም አጋጣሚውን በመጠቀም ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረብኩላት፡፡

ቀጠለችና “ወዴት እየሄድክ ነው?” በማለት ስትጠይቀኝ “ክላስ ስላለኝ ወደዚያ እየሄድኩ ነው” አልኳት፡፡ “ለመሆኑ ደህና ናችሁ?” ስላት “እኛ ደህናን፡፡ አንተስ?” ካለች በኋላ በማከታተል ዐይን ዐይኔን እየተመለከተች ኃዘኔታ በተመላበት ሁኔታ “ባለፈው ሳምንት ልናገኝህ ፈልገን ስንደውልልህ ፖሊስ ጣቢያ መታሰርህን ሰማን፡፡ ለመሆኑ በምን ምክንያት ነው?” በማለት ያልጠበቅኩትን ጥያቄ አቀረበችልኝ፡፡ እኔም እንዴት ልትሰማ ቻለች? በማለት ነገሩ እየገረመኝ “አይ በቀላል ነገር ነው፡፡” ስላት “ታዲያ መቼ ነው የተፈታኸው?” በማለት በድጋሜ ጠየቀችኝ፡፡ “እንዴ ለመሆኑ መታሰሬን ማን ነገረሽ?” በማለት ስጠይቃት “ባለፈው ሳምንት ሻይ ቡና ልንልህ ደጋግመን ስንደውል እህትህ በአጋጣሚ ፖሊስ ጣቢያ መታሰርህን ነገረችን” አለች፡፡ እኔም “ለመሆኑ ከእነማን ጋር ነው ልትጋብዙኝ የነበረው?” በማለት መልሷን ስጠብቅ “እኔ፣ ሔርሜላና ሌላዋ ጓደኛችን” በማለት ስትመልስልኝ ‹ሔርሜላ› የሚለውን ቃል ስሰማ በዚያ ቅጽበት የልቤ ምት ሲጨምር ተሰማኝ፡፡ ወዲያው እንደምንም ለመረጋጋት እየሞከርኩ “ታዲያ አሁን ሔርሜላ የት አለች?” ስላት ‹‹እሷ ክላስ ስላላት እየተማረች ነው፡፡›› አለችኝ፡፡ እኔም ‹‹ለመሆኑ የምን ተማሪ ናት?” በማለት ጠየቅኳት፡፡ ወዲያው የኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ ሁለተኛ ዓመት ተማሪ መሆኗን ነገረችኝ፡፡ አሁን በመጠኑ አደብ እየገዛሁ ስመጣ እንዳትታዘበኝ በማሰብ “አንቺስ የምን ተማሪ ነሽ ?” በማለት ለሞራል መጠበቂያ የሚሆን ጥያቄ አቀረብኩላት፡፡ እሷም “ያው እኔም የሂሳብ ተማሪ ነኝ” በማለት እየሣቀች መለሰችልኝ፡፡

ይቀጥላል………

ꙮꙮꙮꙮꙮꙮ

# የመሪነት ብቃት ...

ከገጽ 7 የዞረ

መሪ ለምንድነው የተቋሙ ሠራተኞች አቅማቸውን አሟጠው ለተቋሙ ተልዕኮ ስኬት የማይሰሩት በሚል የሚጨነቀው ግና መልሱ ያልታየው ሰው ነው ይላል ማክስ ዌል::

## ሁለተኛ ደረጃ አመራር: የተከታዮች ፈቃደኝነት የሚስተዋልበት መሪነት

በዚህ ደረጃ ዋነኛው ቀለበት ቅርርቦሽ ነው - የመሪውና የተከታዮቹ:: የተቋሙ ሠራተኞች ኃላፊያቸው የሚለውን የሚፈጽሙት፣ የሚቀበሉት/የሚታዘዙት በፍላጎታቸው ነው:: መሪው በፀኃፊና በፕሮቶኮል ያልታጠረ ከተከታዮቹ ጋር የቀረበ ትስስርና መግባባት ያለው በመሆኑ ተግባራት ይህንኑ የቀለለና ሠላማዊ የሥራ መንፈስ ተከትሎ ይፈጸምለታል:: በዚህ ደረጃ የክፍሉ ሠራተኞች የተመደቡበትን ዘርፍ ስራ ያለማንም ጎትጓች በሚጠበቀው ጥራትና ደረጃ የሚፈጽሙት የኬዝ ቲም አስተባባሪውን ወይም ሱፐርቫይዘሩን ፈርተውት ሳይሆን ባላቸው ግንኙነት ስለሚወዱት ጭምር ነው:: በእርግጥ ሰው የማዘዝና የመቆጣጠር ስልጣን ይዞ መወደድ ፈተና ነው:: እናም ብዙ አለቆች ባይወደዱ አይገርምም:: የሚገርም ነገር ካለ ለምን ሠራተኞቻቸው እንደሚጠሏቸው ለመለየት ጥረት አለማድረጋቸው ይሆናል:: ስለመወደድ ሲነሳ ለመወደድ ተብሎ በሚሰራ መወደድን ማለት ሳይሆን በመርህ በመመራትና አርአያ፣ ደጋፊ፣ ተግባቢና የመሳሰሉትን የሥራ ግንኙነትን የሚያጠናክሩ ተግባራትን ፈጽሞ ከመገኘት ጋር የሚያያዝ ነው:: በዚህ ረገድ ከልምድ የሚታየው ብዙ አለቆች ከሹመታቸው በፊት በርካታ ጓደኛ የነበራቸው ሠዎች ሲሆኑ ቦታዋን እንዳገኙ ወደብቸኝነት ጎዳና የሚገቡበት ሁኔታ መኖሩ ነው - አያያዙን ካላወቁበት::

ከሠዎች ጋር ያለን ቅርርብ ብቁ መሪ ሆነን ለመውጣት ወሳኝ መሆኑን መረዳት ያሻል:: አንዳንዱ ሲሾም አነጋገሩ፣ አካሄዱ፣ ሠላምታ አሰጣጡ ኧረ ምኑ ቅጡ ሁሉ ነገሩ የሚቀየር ራሱን ከሌላ ፕላኔት የተገኘ አድርጎ የሚያይ ይሆንና የመሪነት ቁመናው ገና ከጀምሩ በዜሮ ሊባዛ ይችላል:: በተቃራኒው ነገ የማይቀጥለውን ባህሪ ተላብሶ ኑ ልዘላችሁ የሚለውም ያው ያልታደለው ይሆናል::

መሪነት ተጽዕኖ ፈጣሪነት ከሆነ ባልቀረብነውና በማናውቀው ወገን ላይ ተጽዕኖ መፍጠር የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም - ግብ ግብ እንጂ:: በደረጃ ሁለት ላይ ያለ መሪ አብዛኞቹ የተቋሙ ሠራተኞች ሲያገኙት በቀላሉ የሚያወሩትና የማይሸቀጠቀጡለት እንጂ አየን አላየን ብለው ሾልከው የሚጠፉና ከለላ ፈልገው የሚደበቁት አይሆንም:: በዚህ ደረጃ ያለ መሪ ጥሩ አድማጭ ነው:: ሁሌም በሠራተኛው ማሃል የሚገኝና የሚሉትን የሚያዳምጥ፣ የሚያደርጉትን የሚመለከት፣ በሥራ አካባቢ ያሉ ሁኔታዎችን በአንክሮ የሚከታተልና የሚመዝን ነው:: እናም በማድመጥ፣ የሥራ ሁኔታዎችን በመመርመርና በግንባር ተገኝቶ በመመዘን የሥራ አካባቢ እይታውን ያሰፋል፣ ሁሌም ይማራል:: እናም አውቃለሁ ብሎ አይቀለልም:: እንደአንዳንዶቹ መሪዎችም ቢሮውን የኮንክሪት ምሽግ በማድረግ ራሱን ደብቆና ከሠራተኛው ሸሽቶ የሚኖር ሰው አይሆንም:: መሪነት ማገልገል ነው በሚል "ማን ምን ይፈልጋል?" ሁሌም ተግቶ ያዳምጣል፣ ይታዘባል፣ ለተቋምና ለሠራተኞቹ ስኬት መደላድሉን ለማመቻቸት ሁሌም ይጥራል:: ያሰባቸው ባይሳኩም እንኳ ሠራተኞች ስለሚረዱት ሁሌም አብረውት ናቸው:: ይህ እንግዲህ በጥቅሉ ሲታይ የመሪውን የአስተሳሰብ አድማስ ስፋትና አመለካከቱን የምናይበት ይሆናል ማለት ነው::

## ሦስተኛ ደረጃ አመራር: በውጤት መምራት

በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ አመራሮች ዘርፋቸውን የሚመሩት ራሳቸውን የውጤት ባለቤት አድርገው በማሳየት ነው:: በመሆኑም ዋናው የዚህ ደረጃ ማዕቀፍ ምርታማነት ነው ማለት ነው:: ሠዎች የሚያደርጉት በተግባር ያዩትን እንደመሆኑ መጠን እዚህ ደረጃ የደረሰ መሪ ሠራተኞች በሚጠብቃቸው ልክ ይሆኑለት ዘንድ ራሱ ሆኖ በመገኘት ሞዴልነቱንየማሳየት ኃላፊነቱንየሚወጣ ነው:: ባልደረቦቻችንና ሠራተኞቻችን ዲሲፕሊን እንዲኖራቸው፣ ታማኝ እንዲሆኑ፣ የአገልጋይነት መንፈስ እንዲላበሱ፣ ለተቋም ኃብትና ንብረት እንዲቆረቆሩ ... መሪዎቻቸው ያን ሆነን መታየትና መገኘት ይኖርብናል:: እንደመሪ ያለን ማንነት የምንስባቸውንና የምናበዛቸውን ሠራተኞች ዓይነትም ይወስናል:: የመሪው ውጤታማነት ከላይ ከተጠቀሱ ባህሪያቱ ጋር እየጎለበተ ሲሄድ በሚመራው ዘርፍ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ እያደገና እየጠነከረ መሄዱ የሚጠበቅ ነው:: ይህም የመሪውን በርካታ ፈተናዎች የሚፈታለት ይሆናል:: በጥቃቅን ፈተናዎች የማይቆም እንቅፋትን ጠርጎ መቀጠል የሚያስችል አቅም መገንባት የሚቻለውም በዚህ ደረጃ ላይ ነው::

## አራተኛ ደረጃ አመራር: ሠውን በማልማት መምራት

በዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ መሪ ዋና መገለጫው ሰውን ማብቃት ላይ መላ ጊዜውን ማሳረፉ ነው:: በየትኛው ተቋም ወሳኙ ሃብት ሠው መሆኑ ማንም የሚስማማበት ጉዳይ ነው:: ብቁ ተቋም መፍጠር የሚቻለው ብቁ ሰው እንዲኖር በማድረግ ብቻ ነው:: የተቋሙ አፈፃጸም የሚያድገው በውስጡ ያሉ መሪዎችና ሠራተኞች አቅም በተከታታይ እንዲያድግ መስራት ከተቻለ ነው:: ይህ ሊፈጸም የሚችለው ደግሞ መሪው በሚከተለው የጉዞ ፍኖተ ካርታ ነው::

ማክስ ዌል እንደሚለው ከሆነ ብቁ ሠው በተቋም ውስጥ እንዲኖር ለማድረግ ሦስት መንገዶችን ተከትሎ መስራት ይጠይቃል:: የመጀመሪያው የመግቢያ በሩን ለብቁዎች ብቻ እንዲሆን ማድረግ ነው:: በቅጥርና ምልመላ ሂደት ከዘመድ አዝማድና ትውውቅ እስር አሠራር ወጥቶ ብቃት ያላቸው ዜጎች ተቋሙን እንዲቀላቀሉ ማድረግ ከተቻለ ወደውጤታማነት የሚወስደው አንዱና ዋናው መንገድ ተጠረገ ማለት ይሆናል:: ስለዚህም መሪዎች ወደክፍላቸው የሚመጡ ሠራተኞችን ብቃት በጥንቃቄ መፈተሽ እንዲችሉ ዕድሉ ሊኖራቸውና በአግባቡም ሊጠቀሙበት ይገባል:: አንዳንድ መሪዎች እንደነእከሌ ያሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኔ ክፍል ውስጥ ቢኖሩ ኖሮ ምን ያህል ውጤታማ እሆን ነበር ብለው ሲቆጩ ይታያሉ:: ምርጥ ምርጥ ሠራተኛ ቢኖረኝ ኖሮ ምርጥ የስራ ዘርፍ እሆን ነበር፤ ማንም በአፈፃጸም አይደርስብኝም ነበር ሲሉም ይደመጣል:: ግን እኮ እንዲህ አይነት የሥራ ቡድን ከያዘ ማንስ ቢሆን ምርጥ ለመሆን ምን ይቸግረዋል? ቁም ነገሩ ያለውን ሰው አብቅቶ ውጤታማ ማድረጉና አዲስ የማስገባት ዕድል ሲፈጠርም ምርጡ ሠው እንዲገባ ትግል ማድረጉ ላይ ነው:: ምክንያቱም ወደሥራ ክፍላችንም ሆነ ወደተቋማችን የሚገቡ ሰዎች በቀጣይ ውጤታማነታችን ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉና ነው:: በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር ወይም በሌላ መንገድ የምናመጣው ሰው ምርጥ ከሆነ በአነስተኛ ድጋፍ ምርጥ ሠራተኛ/መሪ መሆን እንችላለን:: በመሆኑም ክፍት የሥራ መደቦችን/የኃላፊነት ቦታዎችን የመሙላት ሥራ ብቁ ሠዎችን የምናቀርብበት ሊሆን ይገባል::

ስኬታማ የሚባሉ ሠዎች ልዩ ችሎታቸውን ተገንዝበው በዚሁ ልዩ ችሎታቸው መጠቀም የሚችሉ ሲሆኑ ስኬታማ መሪዎች የሚባሉት ደግሞ አብረው የሚሰሩ ባልደረቦቻቸውን ልዩ ችሎታ ተገንዝበው እነዚህ ሠዎች በችሎታቸው ልክ ሊሰሩ በሚያስችላቸው ቦታ ላይ የመመደብ ችሎታ ያላቸው ናቸው:: ስኬታማ ሰዎች ራሳቸውን ለውጤታማነት አመቻችተው የሚገኙ ሲሆን ስኬታማ መሪዎች ግን የሠራተኞቻቸውን የተናጠል ልዩ ችሎታ መዝነው በመለየት ውጤታማ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ በሚችሉበት ቦታ ላይ የሚያስቀምጡ ናቸው:: ይህም መሪዎች ሠዎችን በሚመጥኑት፣ በሚገባቸውና አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ በሚችሉበት ቦታ ላይ በማስቀመጥ የላቀ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ዕድል የሚከፍቱ ናቸው:: እናም በዚህ ደረጃ ላይ ያለ መሪ ትክክለኛውን ሰው የመመልመልና የመምረጥ፣ በሚመጥነው ደረጃ ላይ እንዲመደብ የማድረግ እና ጉድለቶቹን እየለየ የመሙላት ኃላፊነት መወጣት የሚችል ነው:: ትክክለኛውን ሠው መምረጥ ብቻውን ብቁ ሠራተኛ መፍጠር ስለማያስችል ደረጃ አራት ላይ የደረሰ መሪ ሠራተኛውን አዲስ ዕውቀት እንዲጨብጥ የማድረግ፣ በጋራ በመስራት እንዲለማመድ የመደገፍ፣ ራሳቸውና ራሳቸው ብቻ እንዲሰሩ በማድረግ የማብቃት ብሎም ከራሳቸው ተሻግረው ሌሎችን በማብቃት ተግባር ላይ እንዲሰለፉ የማድረግ ተግባር የሚያከናውን በመሆኑ ትኩረቱ ሰው ማብቃት ላይ ያነጣጠረ ይሆናል::

## አምስተኛ ደረጃ አመራር: በተገኘ ክብርና ሞገስ መምራት

በዚህ ዕርከን ላይ የደረሰ መሪ ሠዎች የሚለውን የሚሰሙትና የሚያደርጉት ለመሪው ባላቸው ከበሬታና ፍቅር ነው:: ለመሪው የሚሰጠው ክብርና ፍቅር መነሻው ቀደም ሲል የፈጸማቸው ተግባራትና ግለሰባዊ ስብዕናው ነው:: እንደጂም ኮሊንስ አባባል ደረጃ አምስት የሆነ መሪ በተሰማራበት መስክ ሊቅና ዕውቀትንና ክህሎት የተጎናጸፈ፣ በራሱ የሚተማመን፣ ትኅትና የሞላው፣ ተግባር ላይ የሚገኝ፣ የሌሎችን ውጤት ሽርፎ የማይወስድና ለራሱ ዕውቅና ከሚሰራው ይልቅ ሌሎች ይታወቁና ይወደሱ ዘንድ አበክሮ የሚሰራ ነው:: በመሆኑም በዚህ ደረጃ ላይ የደረሱ መሪዎች ለያዙት ስልጣን ምንም አይነት ስስት ስለሌላቸው ተኪዎቻቸውን የሚለዩና በቻሉት ፍጥነት ከነሱ ልቀው እንዲገኙ የሚሰሩ ናቸው::

ከላይ ያለውን ሁሉ በጥሞና ካነበቡ መቼም በልብዎ እኔ በየትኛው ደረጃ ላይ የምገኝ መሪ እሆን? ብለው መጠየቅዎ አይቀርም:: እልፍ ብለውም ራስዎን ከሚያውቁት ሌላ ባልደረባዎ ጋር ሳያነፃጽሩ አይቀርም:: እኔም በዚህ ዙሪያ ሳነብ የገጠመኝ ይኸው ነበርና:: ታዲያ እርስዎ በእርግጥ የትኛው ዕርከን ላይ የሚገኙ ይመስልዎታል? መቼም ሁላችንም ደረጃ አምስት ላይ ብናርፍ አንጠላም፤ ሆኖም በቦታው ላይ መገኘት ብዙ ልፋትና አስተውሎት የሚጠይቅ በመሆኑ በቀላሉ የምናሳካው ሊሆን አይችልም:: እስቲ ራስዎን ለመገምገም ይችሉ ዘንድ ሰንጠረዡን (ምስል አንድ) በመሙላት ትዝብትዎን ያስቀምጡ:: ይህ ራስዎ ስለራስዎ ብቻዎን የሚሰሩት በመሆኑ ሃቁን ለይተው በማስቀመጥ አስቀድመው ዕውነታውን ያግኙት:: ከዚያ በኋላ የሚሆነውን ያደርጋሉ::

ከላይ የተጠቀሰውን ምዘና መነሻ በማድረግ የሚመሯቸው ሠራተኞች/ኃላፊዎች እርስዎን የሚያዩበትን መነጽር ገምተዋል:: በሠራተኞቹ በኩል ያለው የዕይታ መለያየትና በመሪው በኩል ይህንን ልዩነት መሰረት ያደረገ እንቅስቃሴ አለማድረግ ውጤታማነቱን ይወስናል:: የመሪነት ደረጃዎትን ለማሻሻል የሚያደርጉትን ጥረትም የበለጠ ፈታኝ ያደርገዋል:: ያም ሆኖ ግን ስኬታማ ለመሆን የሚችሉት ይህንን ተረድተውና መፍትሄውንም ዘይደው ሲራመዱ በመሆኑ በዕውቀት ለመምራት የቤት ሥራዎን አሁኑኑ ይጀምሩ::

በቀጣይም ከዩኒቨርሲቲው የዕለት ከዕለት አመራር ተግባራት ጋር የተያያዙ ነጥቦችን በማንሳት ሃሳብ የምወረውር ሲሆን ሃሳቦችን ከኛ ተቋም ሁኔታ አኳያ እንዲገመግሙና አስተያየት ካለም በኢ-ሜይል (alebasfaw@gmail.com) ሊደርሰኝ ይችላል:: በአመራርና መሪነት ዙሪያ ካነበብኩትና ካየሁት ቀጣዩን አካፍላችኋለሁ:: **ቸር ይግጠመን!**

| ተ.ቁ. | በቀጥታ እርስዎ የሚመሯቸው ሠራተኞች ኃላፊዎች ስም | ከተጠቀሰው ሠራተኛ/ኃላፊ ምዘና አኳያ እርስዎ የሚገኙበት ደረጃ |
|---|---|---|
| | | |

ምስል 1

# የግጥም ጥግ

## ደናችን

ደኑ ቢቀርባቸው ጦር እየሰበቁ
ጠመንጃ ደግነው እያነጣጠሩ
… ለአደን ተሰማሩ
ነብሩን አቆሰሉ አንበሳ ገደሉ
ለዚህ ተግባራቸው “ዘራፍ ዘራፍ” እያሉ
ሸለሉ አቅራሩ “ጀግናዎች ነን” አሉ፡፡
አባቶች …
ጠመንጃውን እንዳነገቱ መጥረቢያውን ሳሉ
ዛፉን ገነደሱ ጫካ መነጠሩ በእሳት አቃጠሉ
በዚህ ጊዜ ታዲያ አራዊቶች ሁሉ ከሀገር ኮበለሉ፡፡
ልጆች …
በአያቶቻቸው አለማወቅ ተሳለቁ
… አባቶቻቸውን ኮነኑ
ምድሪቷ ተራቁታለችና በእጅጉ አዘኑ
ምንም እንኳን ቢያዝኑም ቁጭት ቢገባቸው
… እርር ድብን ቢሉ ቢያንገበግባቸው
አካፋና ዶማ ማንሳት አቅቷቸው
እነርሱም …
የአባቶች መጥረቢያ የዶለደመውን
ያንኑ አንስተው “ምን አባቱ” እያሉ
ጉቶ እየፈለጡ ከሰል ያከስላሉ
ታዲያስ! የት? የተማሩትን ችግኙን ይትከሉ፡፡
ተስፋ አለ መጭው ዘመን ትውልድ
ስንፍናው ሲለቀው እየገባው ሲሄድ
ከአያት ከአባቶቹ ከስህተት ተምሮ
ይተክላል እፅዋትን ተራራን ቆፍሮ፡፡

## ይፈለጋል …

ማሳው በመታረስ ዘመናትን ፈጆ
ለምነቱን አጥቶ እያደር አረጀ፡፡
ድግሩ ሳይቀየር ማነቆው ሳይላላ
እንቅብ ጥሩ አፍሰን ጐታችን ሳይሞላ
ሞፈር ከቀንበሩ
በበሬው ጫንቃ ላይ እንደተጐተተ
አዲስ ነገር ሳናይ ስንት ጊዜ ሞተ፡፡
ብዙ አፈረ ገፊ ሌጣ እግሩን ሲኳትን
አቀበት ቁልቁለቱን በእንቅፋት ሲነግል
በኑሮ አዙሪት በተስፋ ሲደለል
ስንት አምናዎች ሄዱ ስንት ዘንድሮ መጣ
እልፍ አላፍ … ወዝ በላ ካለበት ሳይወጣ፡፡
ኧረ መላ እንዘይድ መፍተሄ እናምጣ
ድህነት ኃላቀር ከጉያችን ይውጣ!
ለዚህ መፍትሄ ያለው ይፈለጋል ምሁር
ቀን ከለሊት ሳያርፍ ተግቶ የሚመራመር
አዲስ ቴክኖሎጂ ፈጥሮ የሚያበስር፡፡
ተስፋ አለ … ተስፋ አለ በዚሁ በእኛ ቤት
በዕራዶ ሁለት ሺ አስራ ሰባት
… የአዲስ ግኝት ብስራት
ያን ጊዜና ደህና ሁን ድህነት

የአርሶ አደሩ ልፋት፡፡

ከደስታ ተከስተ (BDU Security Service)

## ሰው እና ያስተሳሰብ ልዩነት

ሰው በሰውነቱ ሁሉም ሰው ሰው ነው፣
አፈጣጠሩም በፈጣሪው አምሳልነው፣
በአስተሳሰብ ግን ሰው ከሰው የተለየ ነው፡፡
ሰው ከሰው አስተሳሰቡ የተለየበት፣
ሲተነተን ብዙ ጉድለት አለበት፡፡
የኸውም፡- በመጀመሪያ ከፍጥረቱ፣
ሁለተኛው ከቤተሰብ ያስተዳደግ ጉድለቱ፣
ሶስተኛው ከሱ የተሻለ ጓደኛ በማጣቱ፣
አራተኛው መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ባለማግኘቱ፣
እነዚህ ናቸው እንቅፋቶቹ ለሱነቱ፡፡
እነዚህን ማስወገድ የሚችለው፣
አለማወቁን አውቆ ከሚያውቁት ሰዎች መማር ከቻለ ነው፡፡
አለማወቁን አውቆ መማር ካልቻለ፣
ማን እንበለው ማንስ ተባለ፡፡
አለማወቁ ይሻላል እሱነቱን፣
ሰው ሁኖ ተፈጥሮ ካላወቀው ሰውነቱን፡፡
እኔስ ማነኝ? ማንነቱን አውቄዋለሁ፣
መልዕክቴ ገንቢ ሳይሆን አፍራሽ ነው ብየዋለሁ፡፡
ቢሆንም አለማወቄን አውቄ እማራለሁ፣
አፍራሽ ሳይሆን ትችት ከሰዎች ጋር አሉ፣
አፍራሽ ትችትና ገንቢ የተባሉ፡፡
ስለዚህ አፍራሽ ትችት ሳይሆን ገንቢውን ይዘን፣
እንማማርበት ገንቢውን ይዘን፣
ከአሉቧልታው ወሬ ከሀሜት እርቀን፡፡

ከ፲አ. ሞላ መስፍን ጩፋ
የባሕር ዳር ከተማ ነዋሪ

## ውድ የናይል ጋዜጣ

አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹሁፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

To follow the latest news about BDU, check out our website:-
**http://www.bduinfo63@bdu.edu.et or http://www.bdu.edu.et**
facebook page:- **www.facebook.com/bduethiopia**

# እንግዳችን ...

ከገጽ 9 የዞረ

ልዩነት ነው ማለት ነው።

19 = ዓውደ አበቅቴ ነው። እሱም ከላይ እንዳልነው በየ19 ዓመቱ ይመላሳል።

አበቅቴ (22)+ መጥቅዕ (8) = 30 $\Longrightarrow$ የሁለቱ ድምር ሁልጊዜ

30 ነው። ከ30 አያንሱም ከ30 አይበልጡም። ይህ ዐዋጅ ነው።

2 x 19 = 38 - 30 = 8 $\Longrightarrow$ የ2008 ዓ/ም መጥቅዕ ነው ማለት ነው።

መጥቅዕ ማለት ደወል፣ አሰባሳቢ፣ መጥሪያ እንደማለት ነው። ከዕለታት ተውሳክ ጋር እየተደመረ ዕለታትንና አጽዋማትን ያስገኛልና።

ስለዚህ የ2008 መጥቅዕ 8 በመሆኑ የተነሣ በጥቅምት ይውላል። ምክንያቱም እንዲህ የሚል ዓዋጅ ስለአለ ነው። (ከ14 በታች የሆነ መጥቅዕ በጥቅምት ይውላል። ከ14 በላይ የሆነ መጥቅዕ በመስከረም ይውላል)። የ2008 ጥቅምት ሰኞ ይብታል። ዕለታት ተውሳክ አላቸው። ይኸውም የቅዳሜ 8፣ የእሑድ 7፣ የሰኞ 6፣ የማክሰኞ 5፣ የረቡዕ 4፣ የሐሙስ 3፣ የዓርብ 2 ተውሳከ አላቸው። በዚህ መሠረት የዕለት ተውሳክ ከዘመኑ መጥቅዕ ጋር ሲደመር = መባጃ ሐመር ይሆናል።
መባጃ ሐመር $\Longrightarrow$ መጥቅዕ ሲደመር የዕለት ተውሳክ (8+6) = 14 ስለዚህ የ2008 መባጃ ሐመር 14 በመሆኑ የካቲት 14 / 2008 ዓ.ም በዕለተ ሰኞ የነነዌ ጾም ትገባለች ማለት ነው። ከዚህ በኋላ 14 ከበዓላትና ከአጽዋማት ተውሳክ ጋር እየተደመረ አጽዋማትና በዓላት ይወጣሉ። ይህ የፀሐይና የጨረቃ አቆጣጠር የኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው።

2. የአውሮፓ አቆጣጠር ግን በጨረቃ ብቻ ነው። ለምሳሌ በእኛና በእነሱ መካከል የ8 ዓመት ልዩነት አለ። ከላይ ስናየው ይኸውም 2008 + 8 = 2016/15
2016 በ19 ሲቀመር (2016÷19 = 106.105 $\Longrightarrow$ .105 (ቀሪው) አይያዝም።
19 x 106 = 2014 ንኡስ ቀመር ይሆናል። ይህ ከዓመተ ምሕረቱ ሲቀነስ ወንበሩ ይገኛል።
2016 — 2014 = 2 ወንበር $\Longrightarrow$ ከላይ እንዳየነው ወንበሩ አንድ ዓይነት ሆነ ማለት ነው።
2 x 11 = 22 $\Longrightarrow$ የ2016 አበቅቴ መሆኑ ነው።

2 x 19 = 38-30 = 8 $\Longrightarrow$ የ2016 መጥቅዕ ነው ማለት ነው።
አበቅቴ + መጥቅዕ = ሠላሳ፣ 22 + 8 = 30 $\Longrightarrow$ ዐዋጅ ነው።
መጥቅዕ 8 በጥቅምት ይውላል እሱም ጥቅምት 8 ቀን ነው። ዕለቱም ሰኞ ነው። የሰኞ ተውሳክ 6 በመሆኑ 6+8 = 14 $\Longrightarrow$ መባጃ ሐመር ይባላል። በዚህ መሠረት ነነዌ የካቲት 14 ቀን 2016 ዓ.ም ትውላለች ማለት ነው። ሌላው ሁሉ ከላይ በሰንጠረዥ እንደተገለጠው ነው። ስለዚህ በአውሮፓና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ልዩነት የአቆጣጠር ዘዴ ልዩነት እንጂ የዘመን ልዩነት የለም ብለው የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የሚናገሩት ለዚህ ነው። እኛ በፀሐይና በጨረቃ ስንቆጥር እነሱ በጨረቃ ብቻ ስለሚቆጥሩ ነው።

ናይል፡ መስከረምና አዲስ ዓመት ለምን ተገናኙ?
ዶ/ር ሙሉቀን፡ በመሠረቱ ዘመን ተመላላሽ ወይም ዞሮ ገጠም በመኾኑ እንደ ክብ መሰል ነገር ነው። ከየትኛውም መጀመር ይቻላል። ብዙዎቹ ከተማ የተመሠረተበትን፣ ንጉሥ የነገሠበትን፣ ሌላም የተለየ ክሥተት የታየበትን መነሻ ያደርጋሉ። መስከረምን እኛ ብቻ ሳንሆን እስርኤልም፣ ግብፅም፣ ሶርያም ዘመናቸዉን ይለውጡበታል። ሃይማኖታዊ ትርጉም ቢኖረውም መስከረም የብርሃኑና የጨለማው ርዝመት እኩል የሚሆንበት ወይም ፀሐይ አናት ላይ የምትሆንበት ወር ነው። ለዚያም ሊሆን ይችላል። ሌላም ምክንያቶች ሊኖሩት ስለሚችል ብዙ ማጥናትንና መመራመርን ይጠይቃል። ሌላው ከስሙ አንፃር ብንሔድ መስከረም ማለት ማግስተ ከርም ማለት ነው። ይህም የክረምት ማግስት እንደ ማለት ነው። ክረምት በጎርፉ፣ በዶፉ፣ በበረዶው፣ በማዕበሉ፣ በውኃ ሙላቱ፣ በብርዱ አስቸጋሪ ወቅት ከመኾኑም በላይ በሀገራችን የፊቱ ያለቀበት የኋላው ያልደረሰበት፣ ላዩ ባሕር ውስጡ ሣር የሆነበት የጭንቅ ጊዜ ነው። ይህ በዓመተ ኵነኔ፣ ዓመተ ፍዳ ይመስላል። በክረምት ማግስት (መስከረም) ክረምቱ የሚያበቃበት፣ ምድር በአበባ የምታሽበረቅበት፣ አንዳንድ እሸቶች የሚደርሱበት፣ ተስፋ የሚለመልምበት፣ አዲስ ነገር የሚታይበት ወር በመሆኑ በዓመተ ምሕረት፣ ተመስሏል። ኀለፈ ክረምት ቆመ በረከት (ክረምት አለፈ በረከት ተተካ) ተብሎ የሚዘመርበት ወር ነው። በትክክልም ዓመተ ምሕረትን ይመስላልና ነው።

ናይል፡ አዲስ ዓመትና ባህላዊ አለባበስ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል?
ዶ/ር ሙሉቀን፡ በአዲስ ዓመት የባህላዊ አለባበስ የተለመደ ነው። ምክንያቱም ከተፈጥሮ የተማርነው ነው።
1ኛ ዘመኑ ከዘመነ ብሉይ ወደ ዘመነ ሐዲስ ተለውጧል። ዓመተ ፍዳዉ፣ ዓመተ ኵነኔዉ ወደ ዓመተ ምሕረት ተለውጧል።
2ኛ መሬት የተለያዩ ኅብረ ቀለማት ባለዉ አበቦች የምትፈካበት ወቅት በመሆኗ ሰዎችም አዲሱን ዓመት አዲስ ለብሰው ይቀበሉታል። እኛም ታድሰናል፣ ካለፈው ስሕተታችን ተምረናል፣ አዲስ ሕይወት ጀምረናል ለማለት ነው። በክረምት ያልነበሩ አበቦች፣ አንዳንድ የሚበሉ እሸቶች ሁልግዜ በመስከረም ስለሚደርሱና ያልደረሱትም እንደሚደርሱ ተስፋ ስለሚጣልባቸው በአጠቃላይ አዲስ ነገር የሚታይበትና በትክክል ከነበረው ዓመት የተለየ ሆኖ ስለሚመጣ ልዩ ነው። በአውሮፓውያን አዲስ ዓመት ይህ አይታይም። ክረምት በመሆኑ ክረምቱ እየከበደ የሚሄድበት የመከራ ወቅት እንጂ አዲስ ነገር የለበትም። የእነሱ ዕፅዋት እንዲያውም እንኳን ሊያብቡ ቅጠላቸው በሙሉ ረግፎ ግንዳቸው ብቻ የሚቆሙበትና የተኮነኑ ነፍሳት የሚመስሉበት ወቅት ነው።
የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት አዲስ ነገር ይዞ ስለሚመጣ ከላይ እንዳልነው ልክ እንደ መሬት ሰዎችም የተለያየ ኅበረ ቀለማት ያላቸውን ልብሶች ለብሰው ይታያሉ። በተለይ ነጭ አበቦችን በመምሰል ፈካ ብሎ መታየት ባህላችን ስለሆነ ነው። የሰው ልጅ የሚፈካው የሚፈነድቀው በተፈጥሮው በነጭ ነገር ነው። ለምሳሌ የምንፈካበት፣ የምንስቅበት፣ የምንፈነድቅበትም ጥርሳችን ነጭ ነው። ይህ የደስታ፣ የብርሃን ምሳሌ ነው።
አዲስ ዓመት ከላይ እንደተገለጠው ያልነበሩ ተስፋ ሰጭ ምልክቶች የሚታዩበት፣ የሰው ልጅ ካለፈው ብዙ ነገሮችን ተምሮና አዲስ የኾነ የአኗኗር ዘዴን ዐቅዶ የሚንቀሳቀስበት እንዲሁም የተሻለ ውጤት አገኝበታለሁ ብሎ በሙሉ እምነት የሚነሣበት በመሆኑ ጤነኛ የሆነ ሰው ሁሉ የተሻለ ነገር አገኛለሁ ብሎ ተስፋ የሚያደርግበት ዓመት ነው። በዓለማዊ ሕይወትም በመንፈሳዊ ሕይወትም 2ኛ ላለመሳሳትና የተሻለ ነገር ለማግኘት ጥረት የሚደረግበት በመሆኑ ተስፋ ሰጭ ነው።

ናይል፡ በመጨረሻ የሚሉት ነገር ካለዎት ዕድሉን እንስጥዎ።
ዶ/ር ሙሉቀን፡ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የደስታ፣ የስኬት የፍቅር እና መልካም የሥራ ዘመን እንዲሆንልን ለመላው የዩኒቨርሲቲያችን ማኅበረሰብ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በዓባይ የባሕልና ልማት ጥናትና ምርምርና በእራሴም ስም መልካም ምኞቴን ለማስተላለፍ እወዳለሁ። መልካም አዲስ ዓመት!

ናይል፡ ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ በመሆንዎ የአክብሮት ምስጋናችንን እናቀርባለን።

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2007 ዓ.ም በከፊል (በፎቶ ማህደር)



HE Patricia M. Haslach, U.S. Ambassador to Ethiopia at BDU

ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት አዘነ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ኮሌጅ በባዮሎጅ ት/ክፍል መምህርና ተመራማሪ በዩኒቨርሲቲው ታሪክ 3ተኛ የሆነውን የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ አገኙ





STEM Incubation Center inauguration at Dilchibo School, Bahir Dar





House of People's Representatives Human Resource Standing Committee interacting with BDU top management to discuss on teaching-learning, research and community services activities of the university







BDU signed Memorandum of Understanding with different institutions

African Universities Presidents and Vice-chancellors made debate on "Secularism and Politicized Faith in Africa" at Bahir Dar University





ጎህ ማተሚያ ቤት ታተመ